# አዲስ ዘመን

እፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 229 ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ያደርጋል

### - ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም በአዲስ አበባ እየተካሄደ ይገኛል



ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሴ

አቶ አህመድ ሺዴ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለማስተዋወቅ ያለመ «ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023» ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም «በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረግ በልጽጉ - ማራኪ የኢንቨስትመንት አማራጮች ያሏት ምድር» በሚል መሪ ሃሳብ መካሄድ ጀምሯል፡፡

በፎረሙ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴ እንደገለጹት፣ መንግሥት በርካታ ፈተናዎችን ተቋቁሞ


በኢትዮጵያ ኢንቨስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## ከሚያዝያ 14 ቀን ጀምሮ ወደትግራይ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል

### - ተጓዦች ያለምንም ችግር አገልግሎቱን እያገኙ መሆኑን ገልጸዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ወደትግራይ ክልል የሚደረገው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ከሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እየተሰጠ መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር አስታውቋል።

በሕዝብ ትራንስፖርት ወደትግራይ ክልል የሄዱ ተጓዦች ያለምንም ችግር አገልግሎቱን እያገኙ መሆኑን ገልጸዋል።

ለትግራይ ተጓዦ በቀን በአማካይ አምስት አውቶቡሶችን እየተጠቀመ መሆኑን ሰላም የሕዝብ ማመላለሻ አክሲዮን ማህበር አስታወቀ።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትሩ አቶ አለሙ ስሜ (ዶክተር) ከሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትግራይ ክልል የሕዝብ ትራንስፖርት በየብስ በአፋር ክልል እየተሰጠ ይገኛል።

በተጨማሪ በሙከራ ደረጃ በአማራ ክልል ወልድያ መስመር ወደትግራይ የሚደረገውን የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት መስጠት ተችሏል ብለዋል፡፡

ሚኒስትሩ አክለውም በቅርብ ጊዜያት ውስጥ በተሟላ ሁኔታ የትራንስፖርት ስምሪት በመስጠት አገልግሎቱ በመደበኛነት ለመስጠት የዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ


ከሚያዝያ 14 ቀን ጀምር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## «የሰላም ስምምነቱ `ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ` በተግባር የተረጋገጠበት ነው»

### - ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ
### የአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የሰሜኑ ጦርነት እንዲያበቃ በፕሪቶሪያ ያደረገችው የሰላም ስምምነት ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ የሚለው እሳቤ በተግባር የተረጋገጠበት ስኬት መሆኑን የቀድሞው የናይጀሪያ ፕሬዚዳንትና የአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ እንዲሁም የሰላም ስምምነቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኦሌሴጉን ኦባሳንጆ ተናገሩ፡፡

ልዩ መልዕክተኛው ኦባሳንጆ ባለፈው እሁድ በወዳጅነት ፓርክ በተካሄደው የሰላም ስምምነቱ ተሳታፊዎችና አካላት የእውቅና አሰጣጥ መርሃግብር ላይ እንደተናገሩት፣ የኢትዮጵያ የሰላም ስምምነት ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ የሚለውን እሳቤ ወደተግባር


«የሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ብርጋዴር ጀኔራል ተስፋዬ ሀ/ማርያም

## ሪፎርሙ ጠንካራና ኅብረ ብሔራዊ ሠራዊት ለመገንባት ያስችላል

**መዓዛ ማሞ**

በአገራችን ክልሎች ከፍተኛ በጀት በመመደብ በርካታ ቁጥር ያላቸው ልዩ ኃይሎችን በማደራጀት የየክልላቸውን ጸጥታ ሲያስጠብቁ ቢቆዩም የክልል ልዩ ኃይል አደረጃጀት በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እውቅና የለውም፡፡ በዚህ የተነሳም አደረጃጀቱ ላይ የሕጋዊነት ጥያቄና ሌሎች ችግሮች መነሳት ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

የልዩ ኃይል አወቃቀር ብሔር ተኮር በመሆኑ እንደ አንድ አገር ያለውን ሕብረ ብሔራዊ አንድነት ከመጉዳት ባለፈ በክልሎች መካከል የእርስ በርስ ጥርጣሬን በመፍጠር ተገቢ ያልሆነ ፉክክር ሊፈጥር ይችላል የሚለው የብዙዎች ስጋት ነው፡፡

ክልሎች ላደራጁት ትልቅ ቁጥር ያለው ልዩ ኃይል ደመወዝ ለመክፈል እና ለማስተዳደር ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ ሌሎች የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የአቅም ውስንነት እንደሚፈጥርም በብዙዎች የታመነ ነው፡፡


ሪፎርሙ ጠንካራና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ፎቶ - አዩብ ተፈራ

አቶ ካሣሁን ጎፌ

# የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ በአህጉሩ የሚገኙ የንግድ ትስስሮችን ማጠናከር ይገባል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግና ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በአፍሪካ አህጉር የሚገኙ የንግድ ትስስሮችን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነት ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃግብር ትናንት ተካሂዷል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ካሳሁን ጎፌ በመርሃግብሩ ማስጀመሪያ ላይ እንደገለጹት፤ ምርቶች በዓለም ገበያ በብዛትና በጥራት በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግና የንግድ ትስስር ሥራዎችን ላቅ ወዳለ ደረጃ ማሳደግ ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ካሳሁን ገለጻ፤ ለኢትዮጵያ ምርቶች አስተማማኝ የገበያ ዕድሎችን ለመፍጠርና መዳረሻዎችን ለማስፋት ትስስሮችን መፍጠር ወጣኝነት አለው፡፡ የወጪ ምርቶችን ወደተለያዩ የዓለም አገራት በስፋት ለመላክ ቀጣናዊ ትስስርን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

ትስስሩን ለማጠናከር የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ያሉት አቶ ካሳሁን፤ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር በሚደረጉ የልማት ትብብሮች ላይ የተለያዩ ሁለትዮሽ ስምምነቶችን መፈራረሟን አስታውሰዋል።

በዚህም ከዓለም ጋር የሚኖራትን መስተጋብር የተሳለጠ ለማድረግና ለአገሪቱ ምርቶች ሰፊ የገበያ ዕድልን ለመፍጠር የሚስችሉ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን ጠቁመው፤ ስምምነቶቹ ደካማውን የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስር አፈጻጸሙን ለማሻሻል የሚያስችሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን በማጽደቅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እያከናወነች ይገኛል። በተጨማሪ በኢጋድ፣ በምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ አገራት የጋራ ገበያ ኮሜሳ እንዲሁም በዓለም ንግድ ድርጅትና በሌሎች ተቋማት ላይ ትስስሮችን የሚያጠናክሩ ጉልህ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው ብለዋል።

አቶ ካሳሁን እንዳስታወቁት፤ በኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ታሪክ 70 በመቶ መሠረት ያደረገው ከአፍሪካ ውጪ ባሉ የንግድ ግንኙነቶች ላይ ነው። ለወጪ ምርቶች አስተማማኝ የገበያ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ በአፍሪካ አህጉር ያሉ ዕድሎችን በስፋት መጠቀም ይገባል።

በአፍሪካ የእርስ በርስ የአገራት የንግድ ትስስር ገቢ የሚያስገኝ ሰፊ ዕድል መኖሩን ጠቁመው፤ የአህጉሪቷን መልካም ዕድሎችና ጸጋዎችን ለመጠቀም ትኩረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራው ላይ የሚሠራው ትሬድ ማርክ አፍሪካ የተሰኘው ተቋም የኢትዮጵያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ ዕውነቱ ታዬ በበኩላቸው፤ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና አገራት የእርስ በእርስ የንግድና ልማት ትስስር እንዲፈጥሩ የሚያግዝ በመሆኑ የየአገራቱን ልማት ለማሳደግ ይረዳል ብለዋል።

እንደ አቶ ዕውነቱ ገለጻ፤ አህጉራዊ ፕሮግራሙ አፍሪካ በዓለም የኢኮኖሚና የንግድ መድረኮች ላይ ያላትን ተደማጭነትና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ያግዛል፡፡

የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጣና 55 አገራትና ስምንት ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትብብር ማህበራትን በማዋሀድ በዓመት 1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ዶላር የሚንቀሳቀስበት በዓለም ትልቁ የልማት ማዕከል መፍጠር የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

# የአሜሪካ ኤምባሲ ለአፋር ክልል ሰብአዊ ድጋፍን የሚያጅቡ ተሽከርካሪዎችን አበረከተ

**በመሠረት በኃይሉ**



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ ኤምባሲ ለአፋር ክልል የሰብዓዊ እርዳታ የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎችን የሚያጅቡ 10 ተሽከርካሪዎችን አበረከተ።

ትናንት በኤምባሲው በተደረገው የርክክብ ሥነሥርዓት ላይ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ጉዳይ አስፈጻሚ አምባሳደር ትሬሲ አን ጃኮብሰን እንዳሉት፣ አሁን ላይ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረገውን ስምምነት ተከትሎ መልካም ሁኔታ ተፈጥሯል፤ ይህም የሰብአዊ እርዳታ ሥራውን ያፋጥናል።

በአሜሪካ ኤምባሲና በአፋር ክልል በተለይም የሰብአዊ እርዳታ ለተፈናቃዮች፣ ለስደተኞች እና ለተጎጂዎች በማቅረብ በኩል ዓይነተኛ መስተጋብር አለ ያሉት አምባሳደር ትሬሲ፤ የአፋር ክልል በጦርነቱ ክፉኛ የተጎዳ ከመሆኑም ባሻገር ከአንድ አመት በፊት አካባቢው በጦርነት ውስጥ ስለነበር የሰብዓዊ እርዳታ ማቅረብ ላይ አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሮ ነበር ብለዋል።

አምባሳደር ትሬሲ እንደገለጹት፤ የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ ባለፉት ስድስት ወራት ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል። በአካባቢውም ሆነ በመላው ትግራይ የመሣሪያ ድምጽ ቆሟል፣ የሰላም የስምምነት ትግበራ፣ የተኩስ አቁም ስምምነት ተግባራዊ እየሆነ ነው፤ የእርዳታ አቅርቦትም በተለያዩ መንገዶች በጦርነቱ ለተጎዱ አካላት እየቀረበ ነው።

አምባሳደሯ አክለውም አሁን ከክልል ፕሬዚዳንቶች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከፌዴራል መንግሥት እና ከዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር በመተጋገዝ ለአፋር፣ አማራ እና ትግራይ ክልሎች የሰብኣዊ እርዳታው የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ሀጂ አወል አርባ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ድጋፉ ለአፋር ክልል በዓይነቱ የመጀመሪያ መሆኑን አስታውሰው፣ የፖሊስ ዘርፉን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

የአፋር ክልል አሁን ላይ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግ የደረሰበትን ጉዳት በመተው የሰብዓዊ እርዳታ ለትግራይ ሕዝብ እንዲደርስ እያደረገ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ይህ የትግራይ ኮሪደር ከ 600 ሺ በላይ ተፈናቃይ የሚስተናገድበት ነው ብለዋል።

የራስን ችግር ተቋቁሞ ለሚሊዮኖች መድረስ ሰብአዊነት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ ሁሉም ችግር ጊዜያዊ በመሆኑ ሰብአዊነትን ማስቀደም ይገባል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳነቱ ገለጻ፤ የአፋርና የትግራይ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን አስፈላጊው ሥራ ሁሉ ይሠራል፤ አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ የአቅም ውስንነቶችም እንዲቀረፉ ክልሉ ጠንክሮ ይሠራል።

# ተኪ ምርቶችን በብዛት በማምረት ኤክስፖርትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አቶ መላኩ አለበል



አቶ ሙስጠፌ መሐመድ

ጅግጅጋ፡- ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ተኪ ምርቶችን በብዛት በማምረት የውጭ ምንዛሪን ለማዳንና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶች ላይ በመሥራት የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የከተማ አስተዳደሮችና የክልል ቢሮዎች እንዲሁም ተጠሪ ተቋማት የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ ትናንት በጅግጅጋ ከተማ ሲጀመር ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ተኪ ምርቶችን በብዛት ለማምረትና ኤክስፖርትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ከፍተኛ መነቃቃት በመፍጠር ሥራ አቁመው የነበሩ ፋብሪካዎች ጭምር ወደ ሥራ እንዲመለሱ በማድረግ አበረታች ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ጠቅሰው፤ ንቅናቄው እንደ አገር ያለውን መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ችግር ለመቅረፍ ያለመ ነው ብለዋል። ለዚህ ንቅናቄ መሳካት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንደሚጠይቅም ገልጸዋል።

በመሠረተ ልማት፣ በግብዓትና በሰው ኃይል ትስስር ያደረጉ ዜጎች ያሏቸው አገራት እድገታቸውን ማስቀጠል እንደቻሉ ጠቁመው፥ በአገራችንም በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ጠንካራ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ትስስር ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓት በመፍጠር ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲኖር በቁርጠኝነት መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

በየዓመቱ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ሥራ እንደሚፈልጉ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ አምራች ኢንዱስትሪው በሥራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ተኪ ምርቶችን በስፋት ለማምረትና ወደውጭ የሚላኩ ምርቶችን ለመጨመር በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህ ንቅናቄም አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሰራሩ በማድረግ ተጨባጭ ውጤት መመዝገቡን ጠቁመዋል።

በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተኪ ምርቶችን ማምረት ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ወደ ውጭ ከተላኩ የኢንዱስትሪ ምርቶችም ከ226 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል ብለዋል።

በተከናወኑት ሥራዎችም በዘጠኝ ወራት ለ161 ሺህ ዜጎች ሥራ እድል መፈጠሩንም አቶ መላኩ ጨምረው ገልጸዋል።

የትኛውም የልማት እንቅስቃሴ ስኬታማ የሚሆነው አስተማማኝ ሰላም ሲሰፍን ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ በሁሉም ክልሎች ላይ ሙሉ ትኩረታችንን ወደ ልማት ለማዞር የሚያስችል ሰላም ለማስፈን በቁርጠኝነት መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሐመድ በበኩላቸው፤ ኢንዱስትሪ ለአንድ አገር እድገት ወሳኝ ከሆኑ ዘርፎች አንዱ መሆኑን ጠቁመው፤ የአንድ አገር እድገት ከሚለካባቸው መንገዶችም አንዱ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረግ ቀጣይነት ያለው መዋቅራዊ ሽግግር ነው ብለዋል፡፡ ዘርፉ በሚፈለገው ልክ እንዲያድግና ለአገር ኢኮኖሚ እድገት የሚጠበቀውን ያህል ድርሻ እንዲያበረክት ከፍ ያለ ትኩረትና ሥራ እንደሚጠይቅም ገልጸዋል።

በሶማሌ ክልል የኢንዱስትሪ ልማት በሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዳልደረሰ ጠቁመው፤ በቀጣይም የሶማሌ ክልል ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ለወደብ ያለውን ቅርበት ግምት ውስጥ ያስገባ ሥራ መሥራት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

አልሚ ባለሀብቶችም ሶማሌ ክልል በኢንዱስትሪው ዘርፍና ሌሎች ዘርፎች ላይ ያሉ ጸጋዎችን በመጠቀም ክልሉ ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል።

ዜና

# የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ሊጀምር ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

ቢሾፍቱ፡- የአገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ሥራ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ፣ በጋምቤላ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በቅርቡ እንደሚጀመር የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ሂሩት ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ተቋሙን በማስተዋወቅ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና የአሠራር ሥርዓት ላይ ሰነዶችን በማዘጋጀት የዝግጅት ጊዜውን እያጠናቀቀ ነው፡፡ በመሆኑም የተሳታፊ ልየታ ሥራ በቅርቡ በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ጋምቤላ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ይጀመራል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ETHIOPIAN NATIONAL DIALOGUE COMMISSION

የተሳታፊ ልየታው ሥርዓት መዘጋጀቱን የጠቆሙት ወይዘሮ ሂሩት፤ በዚህም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሥራቸው፣ በጾታቸው እና በተለያዩ መለያዎች ይለያሉ ብለዋል። በዚህም ከእድሮች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ከሴቶች፣ ከወጣቶች እንዲሁም ሌሎች ኅብረተሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ ሰዎች በተዘጋጀው የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንደሚመረጡ ገልጸዋል።

አገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ የተግባር ሥራ መጋቢት ወር በድሬዳዋ ከተማ ለመጀመር የታቀደ ቢሆንም በረመዷን ፆምና በበዓላት ምክንያት ጊዜው ተራዝሞ በቅርቡ ከአዲስ አበባ፣ ከደቡብ ምዕራብ እና ከጋምቤላ ክልሎች ጋራ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር አምባዬ ኦጋቶ በበኩላቸው፤ በአራቱ ቦታዎች የተሳታፊ ልየታው ሲጠናቀቅ በሌሎች ክልሎች የተግባር ልየታ ሥራው እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ ሥራው በመጪው ክረምት ይጠናቀቃል ብለዋል። ተሳታፊዎች የሚለዩበት ሥርዓት የክልሎቹን ነባራዊ ሁኔታ እንዲያገናዝብ ከክልል ክልል ሊለያይ እንደሚችል ገልጸዋል።

ተሳታፊዎች እንዴት ይለዩ የሚለው ሀሳብ የኮሚሽኑ ብቻ ሀሳብ ሳይሆን የማኅበረሰቡ ሀሳብ ጭምር ተወስዶ የአሠራር ሥርዓቱ እንደሚዘጋጅ የተናገሩት ኮሚሽነሩ፤ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲወከል በጥንቃቄ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ የሚያካሂደው ምክክር ከሌላ አገር ተሞክሮ ወስዶ የሚደግመው ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል የሚወከልበት እና ከታች ጀምሮ ውይይት የሚደረግበት ነው።

የተሳታፊ ልየታ ሥራው ሲጠናቀቅ በቀጣይ የአጀንዳ ልየታ ሥራ እንደሚጀመር ገልጸው፤ በዚህም ሕዝቡ ሊመክርባቸው እና ሊወያይባቸው የሚገቡ አጀንዳዎች ሊመረጡ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

አገራዊ ምክክሩ ከችግር እና ከግጭት ልንወጣበት የምንችልበት እንደሆነ በብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የማኅበረሰብ ክፍሎች የታመነበት ነው ያሉት ኮሚሽነር ዶክተር አምባዬ፤ ለስኬቱ ሁሉም ማኅበረሰብ ተሳታፊ እንዲሆን በተለይም የሚዲያ አካላት ስለ አገራዊ ምክክሩ በቂ መረጃ በመስጠት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



# ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለማፍረስ በተጠረጠሩ ግለሰቦች መዝገብ ላይ ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጠ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ፍርድ ቤቱ ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለማፍረስ ሲንቀሳቀሱ ነበር ተብለው የተጠረጠሩት የእነ ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ አውግቸው መዝገብ ተመልክቶ ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይን ጨምሮ በአምስት ተጠርጣሪዎች ላይ የሠራውን የምርመራ መዝገብ ተመልክቶ ብይን ለመስጠት ለነገ ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

ተጠርጣሪ በሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ አውግቸው፣ ፕሮፌሰር ማዕረጉ ቢያበይን፣ አማሃ ዳኘው፣ ሰለሞን ልመንህ እና ሄኖክ አዲስን በሚመለከት መርማሪ ፖሊስ ከዚህ በፊት በተሰጠው የስምንት ቀን የጊዜ ቀጠሮ የሠራውን የምርመራ ሥራ በዝርዝር ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አቅርቧል።

በዚህም ተጠርጣሪዎች ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለመናድ በማሰብ በአማራ ክልል ሁከትና ብጥብጥ አመፅ በማስነሳት በንብረትና በሰው ላይ በደረሰ ጉዳት ተሳትፎ እንዳላቸው የሚገልፁ በጥናት የተዘጋጀ የሰነድ ማስረጃዎችን ማግኘቱን አብራርቷል።

ለበጎ አድራጎት እርዳታ በሚል ሰበብ በግልፅ አባላት ተመልምሎ አጣዬ አካባቢ ስልጠና ሲሰጡ እንደነበር የተገኘው ማስረጃ በግልፅ ያሳያል በማለት መርማሪ ፖሊስ ለችሎቱ አስረድቷል።

የተለያዩ የገንዘብ ዝውውሮችን ለማጣራት ለባንኮች ደብዳቤ መጠየቁን እና በተጠርጣሪዎች እጅ የተገኘ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን፣ የተያዙ ቦምቦችንና የጦር መሣሪያዎችን እንዲሁም ሰለሞን ልመንህ እጅ የተገኙ የበርካታ የወጣቶች መታወቂያዎችና ሰነዶችን ሕጋዊነት የማጣራት ሥራ እየሠራ መሆኑን ገልጿል።

እንደ አጠቃላይ ከተጠረጠሩበት ወንጀል ጋር የሚገናኝ የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችን መሰብሰቡን አስረድቷል። ቀሪ የምርመራ ሥራዎችን አከናውኖ ለማቅረብ 14 ቀን እንዲሰጠውም ፍርድ ቤቱን ጠይቋል።

የተጠርጣሪዎቹ ጠበቆች በበኩላቸው ለፖሊስ ከዚህ በፊት የተሰጠው ጊዜ በቂ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተጨማሪ የምርመራ ቀናት ሊሰጥ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል። የተጠርጣሪዎቹ የዋስትና መብት እንዲፈቀድም ጠይቀዋል።

መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ በዋስ ቢወጡ ማስረጃ ሊያሸሹብን ይችላሉ ሲል ስጋቱን ገልጾ የዋስትና ጥያቄያቸውን ተቃውሞ ተከራክሯል።

የግራ ቀኙን ክርክር ያዳመጠው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ብይን ለመስጠት ለነገ ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

# የመልካምነት ተምሳሌት ሆኖ ያለፈው አርቲስት ዘሪሁን የመጨረሻ ሽኝት

ዋቅሹም ፍቃዱ

አርቲስት ዘሪሁን ወዳጆ የአርት ሥራውን በብዛት በአፋን ኦሮሞ ቢያቀርብም ሥራዎቹ በሙሉ ገና በለጋ እድሜ ስለ ሰው ልጆች እኩልነት፣ ነፃነትና አንድነት የሚዘክሩ ናቸው፡፡ አርቲስቱ ሕዝቡን ሲያማርር የነበረውን በተለይ በጉቦ ዙሪያ «የጉቦ ጣጣ ከመንዲ ይውጣ» በማለት ገና በለጋ እድሜው በወቅቱ የነበረውን የጭቆና ሥርዓት በግልጽ የተቃወመ አርቲስት ነበር፡፡ አርቲስቱ የሰው ልጆች እኩልነትና ወንድማማችነት አቀንቃኝ መሆኑ ከመቃብር በላይ ያሉ ሥራዎቹ ምስክር ናቸው፡፡



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አቶ ቀጀሳ መርዳሳ

ዘረኝነትን እንደ የማርያም ጠላት አጥብቆ ስለሚጠላ «እኔ የአንድ ወንዝና የአንድ ወገን ልጅ አይደለሁም» በሚል በጥበብ ሥራው የገለጸ አርቲስት ነው፡፡ የተለያዩ የውጭ አገራትን በመጎብኘቱ እዚያ የመኖር ዕድሉ ሰፊ የነበረ ቢሆንም ወደ አገር በመመለስ ከሕዝብ ጋር የመከራ ትግል በመምረጡ በሕዝብ ልብ ውስጥ የወርቅ ሐውልት መሥራት ችሏል፡፡

አርቲስት ዘሪሁን የፊውዳል ሥርዓትን በግንባር የተፋለመ፣ ደርግም ወደ ሥልጣን ሲመጣ «መሬት ለአራሹ» የሚለው መፈክርና አንዳንድ ለውጦቹን አስመልክቶ እንደታሰቡ ተስፋ የሚጣልባቸው ለውጦች አለመሆናቸውን ገና በጅምሩ ተገንዝቦ በጥበብ ሥራ እርቃናቸውን ያስቀረ ጥበበኛ አርቲስት መሆኑን የተናገሩት ደግሞ የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳ ናቸው፡፡

አርቲስቱ ከአንጋፋዎቹ የኦሮሞ አርቲስት እንደነ እልፍነሽ ቀኖ፣ ታደሰ ደበላ፣ አብተው ከበደ፣ ተርፋሳ ምትኩና ሰለሞን ደነቀ ጋር በመሆን የወለጋ ባህላዊ ኪነ ጥበብ ቡድን በማቋቋም «ኑ ከማሳችን አረም እናርም» በማለት ሕዝባዊ ትግል ዳር ያደረሰው ድንቅ አርቲስት እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

መለያየት፣ ዘረኝነትና ክፋት ለሰው አንድነትና ወንድማዊ ሕብረት ጠንቅ በመሆናቸው በአርቲስቱ ዘንድ እጅግ የሚጠሉ አስነዋሪ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን አይደፈሬ በሚባሉት ዘመናት እንኳ ለእውነትና ለሕብረት ለአንዲት ሕይወቱ ሳይሰስት በመታገሉ አብዛኛውን የሕይወት ዘመኑን በእስር ያሳለፈ አርቲስት ነበር፡፡ በመሆኑም «በምንኖረው አጭር ዕድሜ ውስጥ መልካምና ዘላለማዊ ሥራ መሥራት እንደሚቻል ከዘሪሁን እንማር» በማለት አቶ ቀጀላ ሐሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

አርቲስት ዘሪሁን አስቸጋሪ ውጣውረዶችን ያለፈ፣ ለራሱ ያልኖረና ሙሉ ጊዜውን ለሕዝብ ትግል መስዋእት ያደረገ አርቲስት ነው ያሉት ደግሞ የጨፌ ኦሮሚያ አፈ ጉባዔ ወይዘሮ ሠዓዳ አብዱራሂማን ናቸው፡፡ አክለውም የነበረውን የጭቆና ሥርዓት ለመገርሰስ በመረዋ ድምጹ ትውልዱን ያስታጠቀ፣ በቅኔ በተሞሉ ግጥሞቹ ሕዝቡን ከዳር እስከ ዳር በማነሳሳት ዛሬ ለታየው ለውጥ የራሱን ትልቅ አሻራ ያስቀመጠ አርቲስት በመሆኑ በሥራው ሁሌ ይታወሳል ብለዋል፡፡

አርቲስቱ የታገለለትን ዓላማ ዳር ለማድረስ ዛሬ ከትውልዱ የሚጠበቀው በአንድነት፣ በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ ለውጡን ዳር ለማድረስ መትጋት ነው፡፡ የክልሉ መንግሥትም የሕይወት ዘመናቸውን ለሕዝብና ለአገር የቆሙና የሰሩ ባለውለታዎች እንዲሁ እንደማይተዉና ከሕዝቡ ጋር በመሆን ልጆቻቸውን ከማሳደግ በተጨማሪ መልካም ሥራቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ነው የተናገሩት፡፡ ለአገር መልካም ሥራ ሠርተው ግን ደግሞ ችግር ላይ ወድቀው ያሉ ባለውለታዎች ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን በመሆን ውለታ ከፋይ እንዲሆንም ወይዘሮ ሠዓዳ ጠይቀዋል፡፡

«አርቲስት ዘሪሁን ለሁሉም የሰው ልጅ ድምጽ የነበረውና ማንም ያልደፈረውን ጭቆና በጥበብ ሥራው የደፈረ ጀግና አርቲስት ነው፡፡ ዘሪሁን በሥራው ህያው ስለሆነ ሞቷል አይባልም፡፡ ወደ እረፍቱ የተደረገው የጀግና ሽኝት በሥራው ስለሆነ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ከዚህ ብዙ ነገር እንደሚማሩ ሙሉ እምነቴ ነው» ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳዊት ይፍሩ ናቸው፡፡

አርቲስት ዘሪሁን ለራሱና ለቤተሰቡ ያልኖረና ለምድራዊ ሀብት አንድም ቀን ያልተጨነቀ፤ ነገር ግን በዚያው ልክ ያልተደረገለት አርቲስት ነው ያሉት ደግሞ የአርቲስቱ ባለቤት ወይዘሮ አላንቱ ገመቹ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በተለይ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ለአርቲስቱ ያደረጉትን ድጋፍም ወይዘሮ አላንቱ አመስግነዋል፡፡

የአርቲስቱ ሥራዎች ከመቃብር በላይ ቢሆኑም እሱ ግን ባደረበት ሕመም በሕንድ አገር በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ሕመሙ ስለጠናበት ሚያዝያ 15 ቀን 2015 ዓ.ም በ63 ዓመቱ ለሞት እጅ ሰጥቶ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 የፌዴራልና የክልል አመራሮች፣ ወዳጅ ዘመዶቹና የአርቲስቱ አድናቂዎች በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል፡፡

# ሪፎርሙ ጠንካራና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በልዩ ኃይል አደረጃጀት ላይ የሚነሱ ችግሮችን እንደሚፈታ በታመነበት የጸጥታ ኃይል የሪፎርም ሥራ ከሰሞኑ የክልል ልዩ ኃይልን እንደገና በማደራጀት ሕገ መንግሥቱ እውቅና ወደሚሰጣቸው መከላከያ፣ ፌዴራል እና መደበኛ ፖሊስ እንደየምርጫቸው እንዲገቡ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ልዩ ኃይሉን እንደገና ማደራጀት ፋይዳው የጎላ መሆኑን በመንግሥት በኩል በተከታታይ ማብራሪያዎች ሲሰጡበት ሰንብቷል፡፡

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ የክልል ልዩ ኃይል በአገራችን በነበረው ጦርነት ለመከላከያ ሠራዊት ዕገዛ በማድረግ አገርን ከመፍረስ አደጋ በማዳን እንቅስቃሴ ውስጥ ጥሩ ድርሻ ያበረከተ ቢሆንም በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና እንደሌለው እና ጎጂ ጎኑ እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደሚሉት የልዩ ኃይል አደረጃጀት በክልሎች መካከል መፋጠጥ ከማምጣት ባለፈም ፖለቲከኛው መጠቀሚያ እያደረገው ነው፡፡ በየቦታው ከሚያጋጥሙ ግጭቶች፣ ስደት እና ሞት ጋር በተያያዘ ሕዝቡ አደረጃጀቱ እንዲፈርስ ሲጠይቅ እንደነበር አስታውሰው፤ የኢትዮጵያን አንድነት የሚጎዳ በመሆኑ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጭምር በተደጋጋሚ እንዲፈርስ ከመጠየቅ ባለፈ ለምርጫ ቅስቀሳ ጭምር ሲጠቀሙበት እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ክልሎች ከልማት ቀንሰው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለልዩ ኃይል ደመወዝ እና የተለያዩ ወጪዎች እንደሚያወጡ ጠቁመው፤ የልዩ ኃይል እንደገና መደራጀቱ ክልሎች ለልዩ ኃይል ሲያወጡት የነበረውን ወጪ በማስቀረት ልማት ላይ እንዲያተኩሩ ከማስቻሉም በላይ እርስ በርስ ሊገቡባቸው የሚችሉትን አላስፈላጊ መፋጠጥ እንደሚያስቀርም አብራርተዋል፡፡

የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ የኃይል አገነባቡ ብሔር ተኮር በመሆኑ አገር አቀፍ የሆነውን የሕዝቦች አብሮ የመኖር እና አንድነት የሚሸረሽር በመሆኑ አወቃቀሩን ማስተካከል እና ሥርዓት ማስያዝ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደገና የማደራጀቱ ሥራ የተገባበት ለረጅም ጊዜ ጥናት ተደርጎበት፣ እኩል በጋራ እየተፈጸመ እንደሆነ ጠቁመው፤ ሪፎርሙ ዓላማው በኢትዮጵያዊነት የተገነባ ለሁሉም ሕዝብ እኩል የሆነ፣ ለኢትዮጵያዊነት ጠቅላይ ግዛት ሊመች የሚችል ችሎታ ያለው በቴክኖሎጂና በትጥቅ እንዲሁም በአሠራር የዘመነ የጸጥታ ግብረ ኃይል ማደራጀት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በዋናነት የሚያጠነጥነው የአገሪቷ ግዛት አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ የሕዝቦች ደህንነት መነሻ አድርጎ መጠበቅ እና መከላከል ላይ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን የሰጡት የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ወለድ ጦር አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በበኩላቸው የልዩ ኃይል አደረጃጀት ከስሙ ጀምሮ አወቃቀሩ ችግር የነበረበት መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን እንደገና በመደራጀት ወደ ሕጋዊ መስመር መግባቱ ይበል የሚያሰኝ እና እንደ አገርም በርካታ ጥቅሞች ያሉት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም እንደሚሉት፤ የልዩ ኃይሉ እንደገና መደራጀት የሠራዊቱን ቁጥር በማሳደግ ተጨማሪ አቅም እንዲፈጥር በማድረግ ጠንካራ አገራዊ የመከላከያ ሠራዊት መገንባት ያስችላል፡፡ ሕብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር ረገድም የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡

ልዩ ኃይሎች እንደገና ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅዳቸው መዋቅሮች ሲደራጁ በቂ ስልጠና ማግኘት አለበት የሚሉት ብርጋዴር ጄኔራሉ፤ ጥራት ያለው፣ በወታደራዊ ሳይንስ ዓቅሙ የጎለበተ፣ ጠንካራ የአካል ብቃት ያለው፣በሥነ ሥርዓት የታነጸ፣ በግልም በቡድንም ሆኖ ግዳጅ መወጣት ዓቅም ያለው እና ከምንም በላይ የአገር እና የሙያ ፍቅር ያለው እንዲሆን ሠራዊቱን ከመቀላቀሉ በፊት በቂ ስልጠና ሊሰጠው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የቀድሞ ጦር ሠራዊት አባል የሆኑት ብርጋዴር ጄኔራል አሰፋ አዕፈሮም በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ሁሉንም የሚወክል ሠራዊት ሊኖራት ይገባል፡፡ ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት ሠራዊቱን ከማጠናከሩም ባሻገር በብሔር ተዋፅዖ ምሉዕ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በአንድ አገር ሊኖር የሚገባው አንድ የመከላከያ ሠራዊት እንደሆነ የጠቆሙት ብርጋዴር ጄኔራል አሰፋ፤ ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ሥራው ሕዝቡ በልበ ሙሉነት የራሱ ሠራዊት እንደሆነ እንዲያስብ ዕድል የሚፈጥር እና ዋስትናውም እንዲረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ በትኩረት ሊሠራ የሚገባው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ልዩ ኃይልን አዲስ ተልዕኮ በመስጠት መከላከያን የማጠናከር ሥራ የመንግሥት ኃላፊነት መሆኑን ጠቁመው፤ ሆኖም የሚደረገውን ነገር ሕዝቡ እያወቀው እና ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ እየተሰጠ ሊሆን ይገባዋል ብለዋል፡፡

የልዩ ኃይል እንደገና መደራጀት አባላቱን ለበለጠ ኃላፊነት ያጨ፣ ክልሎችን ከትልቅ ወጪ የታደገ፣ ለሠራዊቱ ትልቅ አቅም የሚጨምር እና በዜጎች መካከል የሚኖረውን ሕብረ ብሔራዊ አንድነት የሚያጠናክር እንደሆነ እና ሌሎች በርካታ ፋይዳዎችም እንዳሉት በርካቶች ይስማሙበታል፡፡

# በኢትዮጵያ ኢንቨስት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ቀጣይነት ያለውና የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመገንባት የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመተግበር ላይ ሲሆን ይህም ለግሉ ዘርፍ መነቃቃት እየፈጠረ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት በአግባቡ በመጠቀም ባለሀብቶች ኢንቨስት ቢያደርጉ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥትም አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት አገር ከመሆኗም በላይ ያላት የአየር ንብረት ሁኔታ ለኢንቨስትመንት አመቺ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ካሉ አገራት ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ነው። በአፍሪካ ለኢንቨስትመንት ምቹ ከሆኑ አገራት መካከል ቀዳሚዋና አንዷ ሆናለች። የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቿ አሳታፊና አካታች እንዲሆኑ መንግሥት ጠንካራ ሥራ እየሠራ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች በርካታ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ጨምሯል። ዓለም አቀፍ ንግድን በማሳደግ ኢኮኖሚውን ለማዘመንም እየተሠራ ነው።

በኢትዮጵያ በርካታ የኢንቨስትመንት እድሎች አሉ ያሉት አቶ አሕመድ፣ ኢትዮጵያ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ማለት በአፍሪካ ኢንቨስት ማድረግ ነው ብለዋል። በመሠረተ ልማትም እያደገች በመሆኗ ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኗን ጠቅሰው በቀጣይ ሁለት ቀናት በሚኖሩ ውይይቶች ኢትዮጵያ ስላሏት ሀብቶች ጥሩ ግንዛቤ እንደሚፈጠር ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ በበኩላቸው፤ መድረኩ ለኢትዮጵያ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በኢትዮጵያ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ኮሚሽነሯ፤ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች እየተሻሻሉ ስለመሆኑ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ሰፊ መሠረተ ልማት፣ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሎጅስቲክስ፣ ምቹ ፖሊሲና አምራች የሰው ኃይል ያላት በመሆኗ ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ያደርጋታል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በግብርና፣ በኢነርጂ፣ በቱሪዝም፣ በአይሲቲ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ትልቅ አቅም አላት ያሉት ኮሚሽነር ሌሊሴ፤ እየተሠሩ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በልማት ለመሰማራት ትልቅ ዕድል የሚፈጥሩ ስለመሆናቸው አብራርተዋል። እንዲሁም በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅም በመኖሩ የኃይል መቆራረጥ ችግር እንደማይሆን ገልጸዋል።

ፎረሙ ከትናንትና ሚያዝያ 18 ጀምሮ እስከ 20 የሚቆይ ሲሆን ከመላው ዓለም የተውጣጡ ኢንቨስተሮች፣ የንግድ ተቋማት ኃላፊዎች፣ የፖሊሲ አውጪዎችና ሥራ ፈጣሪዎች እየታደሙበት ይገኛል።

# «የሰላም ስምምነቱ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

መቀየር የቻለ ትልቅ ድል ነው፡፡

የሰላም ስምምነቱ ትግበራዎች መጀመራቸው በመንግሥት በኩል ያለውን የሰላም ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ያሉት ልዩ መልዕክተኛው፤ በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የነበረውን ጦርነት ለማርገብና ሰላም ለማምጣት የተሄደበት መንገድ ውጤታማ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደሳቸው ገለጻ፤ ወደ ሰላም ድርድሩ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጥይት ድምጽ እንደሚቆምና ስምምነት ላይ እንደሚደረስ ባለሙሉ ተስፋ እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡

የሰላም ስምምነቱን የተሳካ እንዲሆን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) የነበራቸው ሚና ከፍተኛ እንደነበረ የገለጹት አባሳንጆ፤ የሕወሓት አመራሮችም ለሰላም ስምምነቱ ያሳዩትን በጎ ምላሽ አድንቀዋል፡፡

በፌዴራል መንግሥቱና በሕወሓት በኩል ተፈጥሮ የነበረውን ውጥረት ለማርገብ የተሄደበት ርቀት ሁለቱ አካላት ለሰላምና መረጋጋቱ ሂደት የነበራቸው በጎ ምላሽ የሚደነቅ መሆኑ ገልጸው፤ በኢትዮጵያ መንግሥት እና በሕወሓት በኩል ሰላም ለማምጣት የነበረው አቀባበል መልካም እንደነበር ጠቁመዋል፡፡

በሰላም ስምምነቱ ላይ በጎ ተሳትፎ የነበራቸውን አገራት እና መንግሥታትን ያመሰገኑት አባሳንጆ፤ የሰላም ስምምነቶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ መንግሥት ያደረገውን ጥረት አድንቀዋል፡፡ የሰላም ስምምነቱ ትግበራዎች መጀመራቸው ስምምነቱ ዘላቂነት እንዲኖረው እና በመንግሥት በኩል ያለውን የሰላም ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

በጠፋው የሰው ሕይወት ብናዝንም አሁን ላይ በተገኘው ሰላም ደስተኞች ነን ያሉት አባሳንጆ፤ በሰላም ስምምነቱ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው ቀሪዎቹም ሥራዎች በፍጥነት እንዲፈጸሙ ጠይቀዋል፡፡

የደቡብ አፍሪካ የዓለም አቀፍ ግንኙነት እና ትብብር ሚኒስትር የሆኑት ናሌዲ ፓንዶር በበኩላቸው፤ በኢፌዴሪ መንግሥት እና በሕወሓት በኩል የተደረገው የሰላም ስምምነት ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄን ማምጣት እንደሚቻል ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ጦርነት የእድገት ጸር መሆኑን እና የእድገት ብቸኛው መሠረት ሰላም መሆኑን አፍሪካውያን መረዳት አለባቸው፡፡

ለአፍሪካውያን ምሳሌ የሆነውን የሰላም ስምምነት ታሪካዊ የሚያደርገው ከዚህ ቀደም በቀኝ ግዛት ስር ካልወደቁት አገር የመነጨ መሆኑ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይህ በንግግር ችግሮችን የመፍታት ልምድ በሌሎች የአፍሪካ አገራትም ተወስዶ የዜጎች ሰብዓዊ መብት የሚከበርባት እና ከጥይት ድምጽ የጸዳች አህጉር እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡

በዕለቱ በነበረው መርሃግብር ላይ ለሰላም ስምምነቱ በጎ ሚና የተጫወቱ አካላት እውቅናና ሽልማት የተበረከተላቸው ሲሆን ለሰላም ስምምነቱ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ልዩ መልዕክተኛው ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ ልዩ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

# ከሚያዝያ 14 ቀን ጀምሮ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ናቸው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከአዲስ አበባ መቐለ እንዲሁም ከመቐለ አዲስ አበባ በቀን በአማካይ አምስት አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ሰላም የሕዝብ ማመላለሻ አክሲዮን ማህበር አስታውቋል።

የአክሲዮን ማህበሩ የኦፕሬሽንና ማርኬቲንግ ዘርፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሙሉብርሃን ያለምሸት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባና በመቀሌ በሚገኙ የትኬት ቢሮዎች አማካኝነት ለተጓዦች አስፈላጊው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል።

ወደ ትግራይ ይደረግ የነበረው ጉዞ በጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም ከሚያዝያ 14 ጀምሮ 2015 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት እየሰጠ ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የጉዞ መስተጓጉሎች በመቀረፋቸው አውቶቡሶች በሰላም እየተንቀሳቀሱ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ ሙሉብርሃን እንደገለጹት፤ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱ ከአዲስ አበባ መቐለ ብቻ ሳይሆን ከመቐለም ወደ ሽሬ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

ከአዲስ አበባ ወደ መቐለ እንዲሁም ከመቐለ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዘው የሕዝብ ቁጥር ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጥቷል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ከሕዝቡ ፍላጎት አንጻር ተጨማሪ የአገር አቋራጭ አውቶቡሶች አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የተሟላ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በየቀኑ የሚደረገውን የጉዞ ሂደት እየገመገምን ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

በሕዝብ ትራንስፖርት ከአዲስ አበባ መቐሌ የገቡት አቶ ሀፍቱ ኪሮስ በስልክ እንደተናገሩት፤ በአፋር ሰመራ በኩል ያለምንም የጸጥታ ችግር በሰላም ወደ መቐለ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መጀመሩ የኅብረተሰቡን እንቅስቃሴ ለማሳለጥ ይረዳል። ጉዳያቸውን መፈጸም የሚፈልጉ ዜጎችም ተንቀሳቅሰው ያሰቡበት ቦታ እንዲደርሱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱ መጀመር ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

ሌላኛው ተጓዥ አቶ ዘነበ መሃሪ በበኩላቸው፤ ያለምንም የጉዞ እንግልት ከአዲስ አበባ ተነስተው



በሕዝብ ትራንስፖርት አማካኝነት በሰላም ወደ መቐለ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱ መጀመሩ ለተገልጋዩ ትልቅ እፎይታን የፈጠረ ነው ያሉት አቶ ዘነበ፤ አገልግሎቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ ተጠናክሮ እንዲሄድ ኅብረተሰቡና የመንግሥት አካላት እንዲሁም የትራንስፖርት ማህበራት ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስሰላም እንጀግን!

እኛ ኢትዮጵያውያን በጀግንነት የምንታማ ሕዝቦች አይደለንም። እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ነፃነታችንን አስጠብቀን የቆየነው በብዙ ተጋድሎ በታጀበ የጀግንነት ገድል ነው። ይህ ደግሞ ከእኛ ተርፎ ለጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትግል መነቃቃት የፈጠረ ፤ ብዙዎች በነፃነት አንገታቸውን ቀና አድርገው ኮርተው እንዲኖሩ ያስቻለ የማንነታችን አንዱ ገጽታ ነው ።

የትኛውም ኢትዮጵያዊ ስለ ሃገር እና ስለ ነፃነት ጉዳይ ተነስ ፣ታጠቅ ከተባለ ጨርቄን ማቄን የሚል አይደለም፤ ከዚህ ይልቅ ስለሀገሩ እና ነጻነቱ መሞትን እንደ ክብር የሚቆጥር ነው። በትውልዶች መንሰላሰል ውስጥ የታየውና ትናንትም የተስተዋለው ይሄው ነው። አብዛኛው የታሪክ ትርክቶቻችንም ይህንን እውነታ በደማቅ ቀለሞች የሚያጎሉ ናቸው።

ይህ ታሪካችን ዓለም አቀፍ እውቅና ያተረፈልን የመሆኑን ያህል፣ ስለ ጀግንነታችን ለነፃነት ስላለን ቀናዒነት ብዙ ምስክሮችን የፈጠረልን ያህል፣ በየወቅቱ በሚፈጠሩ ግጭቶች የምንከፍለው ያልተገባ ዋጋ ሃገራዊ ገጽታችን ከጦርነትና ከዚህ ከሚመነጭ ድህነትና ጠባቂነት ጋር ተቆራኝቶ ብሔራዊ ክብራችንን ሲያጠለሽብን ቆይቷል።

ችግሮችን በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብሎ በውይይት መፍታት ባለመቻሉ በሚከሰቱ ግጭቶች ማግስት በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት በመጓዝ፣ የቀደሙት ትውልዶች ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፣ ይህ የተዛባ አስተሳሰብ አሁን ያለውንም ትውልድ ጠልፎት ምንያህል ዋጋ እንዳስከፈለው የትናንቱን ሃገራዊ እውነታ በሰከነ መንፈስ ተመልሶ ማየት ተገቢ ነው።

ችግሮችን ሁሉ በኃይልና በኃይል ብቻ በመፍታት ላይ የተመሠረተው የፖለቲካ ባሕላችን፤ ኃይል አምላኪ ግለሰቦችና ቡድኖችን በመፍጠር፤ ይህንን በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ሥጋና ደም እንዲለብስ በማድረግ፣ ሃገር እንደሃገር ዘላቂ ሰላም እንዳይኖራት አድርጓል። ቂም በቀልና ሴራ የሃገራዊ ፖለቲካው የረጅም ዘመን መገለጫ እንዲሆን አስገድዷል።

ለዘመናት አሸናፊው የአሸናፊነት መሠረቱ የኃይል የበላይነት መሆኑ፤ የተሸናፊውም ሽንፈቱ የኃይል ሚዛኑ መሆኑ ለዘላቂ ሰላም መሠረት መሆን አልቻለም። ከዚህ ይልቅ አሸናፊው አሸናፊነቱን ለማጽናት፣ተሸናፊውን ከሽንፈቱ ወጥቶ በአሸናፊነት ሰገነት ላይ ለመውጣት በማያቋርጥ የደባ እና የሴራ ተግባራት ላይ እንዲቆሙ፤ ተስፋቸውም በዚሁ ላይ እንዲመሠረት አድርጓል ።

በዚህም ሕዝባችን እንዲከፍል የተገደደው ዋጋ ለመናገር የሚከብድና የፖለቲካ ትርክቱ ከፈጠረው የአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት በላይ የሆነ ነው። የትውልዶችን የዘመናት የበለጸገች ሀገር ፈጥሮ እና አይቶ የማለፍ ከፍ ያለ ተስፋ እና ራዕይ ያኮላሸ ፤ ስለነገዎቹን ጽልመት አልብሶ በተሰበረ ልብና መንፈስ ወደ መቃብር እንዲወርድ ያደረገ ነው።

የአንድ ትውልድ ስኬታማነት ዋነኛ መለኪያዎች መካከል አንዱ የሚኖርበትን ዘመን ለመዋጀት ያለው አቅምና ዝግጁነት ነው፤ ከዚህ አኳያ ዛሬ ላይ ያለውን ትውልድ ከተሳሳተ ትርክት ከመነጨ የፖለቲካ ባሕላችን እስካሁን ከከፈለው ያልተገባ ዋጋ በላይ አይገባም። ካለበት ዘመን አንጻር ዘመኑን በሚዋጅ አስተሳሰብ ራሱን ማረቅ ይኖርበታል ።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ ራሳችንን ለሰላም ማጀገን፤ ለዚህ የሚሆን አዕምሯዊ እና መንፈሳዊ ዝግጁነት ማዳበር ይጠበቅብናል። ራስን ከግጭት ነጋዴዎች የጥፋት እና የግርግር ትርክት በመጠበቅ፤ ለራስ፣ ለምኖርበት ማኅበረሰብና ለሀገር ዘላቂ ሰላም በኃላፊነት መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ ዘመኑን መዋጀት ነው ።

ይህንን ማድረግ የቀደሙት ትውልዶችንም ሆነ የራስን ሀገር ለምታና በልጽጋ የማየት ተስፋና ራዕይ እውን ማድረግ የሚያስችል ጠንካራ መሠረት መጣል፤ በግጭትና በጦርነት እንደሀገር የከፈልናቸውን ያልተገቡ ዋጋዎች በተሻለ መልኩ ለመካስ የሚያስችል አዲስ አስተሳሰብና የታሪክ ትርክት ማጽናት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የስፖርት ፌዴሬሽኖች ራሳቸውን ለመቻል ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው

ብርሃን ፈይሳ

ዘመናዊ ስፖርት መዘውተር ከጀመረ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ በተቆጠረባት ኢትዮጵያ፤ የተደራጀና ወጥ የሆነ አሠራር የዘርፉ መሠረታዊ ችግር በመሆን ቀጥሏል። የሕዝባዊና መንግሥታዊ አካላት ኃላፊነቶች መጣረስ ስፖርቱ እንዳያድግ ማነቆ ሆኖት ቆይቷል። በዓለም አቀፍ ውድድሮች የተገኙ ውጤቶችም በጠንካራ መሠረት ላይ የተንተራሱ ባለመሆናቸው ብቅ ጥልቅ በማለት ቀጥለዋል።

በ1990 ዓም በወጣው የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ፤ ‹‹የስፖርት አጠቃላይ እንቅስቃሴ አደረጃጀትና አመራር ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ይደረጋል›› ይላል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሃገሪቷን ስፖርት በበላይነት የመምራት ሥልጣን የሕዝባዊ አካሉ (ክለቦች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና የስፖርት ምክር ቤቶች) ሆኖ መንግሥታዊ አካሉ ሕዝባዊ አካሉን የመደገፍና የማገዝ ሚና እንደሚኖራቸው ይገልጻል። ነገር ግን በ2012 ዓም የተዘጋጀው ሀገራዊ የስፖርት ሪፎርም ጥናት መሠረታዊ ክፍተት መኖሩንና መንግሥታዊና ሕዝባዊ አካሉ አደረጃጀት በመፋለሱ ለያይቶ ለማስቀመጥ አዳጋች እንደሆነ ያስቀምጣል።

በፖሊሲው ላይ የተመላከተው ሃሳብ በሌሎች ሃገራት እየተተገበረ ያለው በቅደም ተከተሉ መሠረት በመሆኑ ስፖርቱ ብቻም ሳይሆን ስፖርቱን የሚመሩት አካላት ጭምር በአቅም የጎለበቱ ናቸው። የመንግሥት ሚና እንደ ኦሊምፒክ፣ የዓለም ዋንጫ፣ የመላ አፍሪካ ጨዋታዎችና የመሳሰሉት ትልልቅ ውድድሮች ሲካሄዱ፤ ሃገር የምትወከልበት እንደመሆኑ ብሔራዊ ቡድኑን መደገፍ ነው። ወደ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ስንመለስ ግን ከፈረሱ ጋሪው ቀድሞ የሕዝባዊ አካሉን ሥራ መንግሥት ሲያከናውን በመቆየቱ የመዋቅር መደበላለቆች ታይተዋል።

መንግሥታዊው አካል (የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር) ከ30 ለሚልቁ የስፖርት ፌዴሬሽኖችና አሶሴሽኖች፣ የጽሕፈት ቤት ኃላፊና ባለሙያዎችን ይቀጥራል፣ በጀት ይመድባል፣ የዓለም አቀፍ ስፖርት ማኅበራት የአባልነት ክፍያዎችን ይሸፍናል፣ ሥልጠናዎችን በአጋርነት ያዘጋጃል፣ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሲካሄዱም የገንዘብ የትጥቅ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ያደርጋል። እንዲያም ሆኖ ግን ፌዴሬሽኖች ራሳቸውን ከመቻል ይልቅ በጎደለው እያማረሩና የመንግሥትን እጅ እየተጠባበቁ ዘመናትን አሳልፈዋል።

እንደሚታወቀው ስፖርት በባሕሪው እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ ዘርፍ ነው፤ በመሆኑም የራስን የገቢ ምንጭ ማፈላለግ የግድ ነው። ምክንያቱም እጅ ሲያጥራቸው ከታዳጊ ፕሮጀክት እስከ ብሔራዊ ቡድን የሚኖረውን ሥልጠና ማሳለጥ፣ የባለሙያዎች አቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ማዘጋጀት፣ በየደረጃው ውድድሮችን ማካሄድ፣ በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ሃገርን መወከል፣... አይቻልም። በዚህም የሚጎዳው ስፖርቱ ብቻ ሳይሆን ስፖርት እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ እንዲሁም የመልካም ገጽታ መገንቢያነቱ ሃገርም ጭምር ነው።

በአንጻሩ ጊዜውን፣ ገንዘቡን፣ እውቀቱን እና ልምዱን ፈሰስ በማድረግ ስፖርቱን ይጠቅማል በሚል የተወከለው የሥራ አስፈጻሚ (ሕዝባዊው አካል) ተሳትፎውን የሚያረጋግጠው ጠቅላላ ጉባኤ ሲካሄድና ዓለም አቀፍ ጉዞዎች ሲኖሩ ነው። ሃገር አቀፍ የስፖርት ማኅበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ፤ ሥራ አስፈጻሚ ማለት አንድን ሃገር አቀፍ የስፖርት ማኅበር የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ለማስፈጸም በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ አካል መሆኑን ይጠቁማል። ይህም ማለት ለሃገርና ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ፤ ስፖርቱን በሃብቱ፣ በእውቀቱና በሙያው መደገፍ የሚችል ግለሰብ ነው። ማኅበሩ የውስጥ ገቢ የሚያሳድግበትን የተለያዩ ሥራዎች መሥራት እንዳለበትም በመመሪያው በግልጽ ተመላክቷል።

ያም ሆኖ አብዛኛዎቹ የሥራ አስፈጻሚዎች እንደ መስቀል ወፍ አልፎ አልፎ ብቅ ከማለት ባለፈ በግል ሥራቸው ላይ የተጠመዱ ናቸው። በመመሪያው የቀድሞ ስፖርተኛ፣ ሙያተኛ አሊያም ለስፖርቱ ጥልቅ ፍቅር ያለው እንዲሆኑ ቢያመላክትም በበርካቶች የሚነሳው ሃሳብ ግን ከዚህ በተቃራኒ ስለ ስፖርቱ እውቀት የሌላቸው መሆኑን ነው። ይህ ከሆነ ስፖርቱን ለመምራት ለምን አስፈለገ የሚለው ጥያቄ ሲነሳ የሚቀመጠው መላ ምት ስፖርቱን እንደ መረማመጃ በመጠቀም የራሳቸውን ጥቅም ማሳደድ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነውም የስፖርት ማኅበራቱ ችግር ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት ወይም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ድርሻ ሳይኖራቸው፤ በመንግሥት በኩል አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቅሬታ ለማሰማትና ለዓለም አቀፍ የስፖርት ማኅበራት ሃገርን ለመክሰስ መሯሯጣቸው ነው። እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት የጥቅም ሽኩቻ ሕዝብ ድረስ የደረሰ፤ መንግሥትም ለመገላገል እጁን ያስገባበት ተደጋጋሚ እሰጣገባም ማስረጃ ነው።

በእርግጥ በባለቤትነት ስሜት ሙሉ ጊዜና ጉልበታቸውን ሰጥተው ስፖርቱን ለማሳደግ የሚለፉ፤ በዚህም ከሃገር አልፎ በአህጉርና ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ሥራ አስፈጻሚ(ቦርድ) ውስጥ የመካተት እድል ያገኙ መልካም ባለሙያዎች ስለመኖራቸው አይካድም። የሚልቁት ግን በሚጠበቁት ልክ ያልተገኙ ስለመሆናቸው አሁንም ድረስ ጉዟቸው የእንፉቅቅ መሆኑ ያሳብቃል። መንግሥትም ፖሊሲውን ከማስተግበር ይልቅ ለዘመናት እነዚህን አካላትና አሠራሩን እሹሩሩ ሲል መቆየቱ ማኅበራቱ ራሳቸውን እንዳይችሉ በማድረግ ረገድ ሚና ነበረው።

አሁን ይህ አሠራር ተቀይሯል፤ ሚኒስትሩ ተግባራዊ ያደረገውን መዋቅር ተከትሎ አብዛኛዎቹ የስፖርት ማኅበራት ድንገት ከጎጆው እንደወደቀ ጫጩት ግራ መጋባት ውስጥ ገብተዋል። በፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫ መሠረት ማኅበራቱ ራሳቸውን ችለው ከመንግሥት እገዛ እንዲላቀቁ፣ ባለሙያዎችን እንዲቀጥሩና የራሳቸውን ቢሮ እንዲያደራጁ እየተደረገ ነው። አስቀድሞ ራሳቸውን የቻሉ 6 ማኅበራት (እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ኦሊምፒክ ኮሚቴ፣ ሞተር ስፖርት፣ ወርልድ ቴኳንዶ እና ፈረስ ስፖርት) ብቻ ነበሩ። መዋቅሩን ተከትሎም ከፊሉ ተቀላቅለዋቸዋል፤ የተቀሩት ደግሞ በአንድ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ስር በጀታቸው 50 ከመቶ ቀንሶባቸው ራሳቸውን ለመቻል ጥረት እንዲያደርጉ ጊዜ ተሰጥቷቸዋል።

ይህ ሁኔታ የከበዳቸው ፌዴሬሽኖች አሁንም ቅሬታዎችን በማንሳት ላይ ይገኛሉ። ቀድሞ የነበረው የውድድር ተሳትፏቸውም ይበልጥ እየቀነሰ መጥቷል። ጫጩት እንደመሰሎቿ መብረር እንድትችል ከጎጆዋ በቅድሚያ የምትገፋት እናቷ ስትሆን፤ ይህም የጭካኔ ሳይሆን ራሷን እንድትችል ለማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው። መንግሥትም ፖሊሲውን እውን ለማድረግ ይህንኑ መንገድ መርጧል፤ ስለሆነም ማኅበራቱ መፍጨርጨር ያለባቸው ራሳቸውን ለመቻል እንጂ ለክስና ለቅሬታ መሆን የለበትም። ማኅበራቱን መምራት የሚገባቸው የሕዝባዊ አካላት ተወካዮችም አሁን ትክክለኛ ሚናቸው የሚወጡበት ጊዜ የመጣ ይመስላል።

በመሆኑም ሕዝብ የመረጣችሁ፣ ስፖርቱን ታሳድጋላችሁ የሚል ተስፋ የተጣለባችሁና አቅም ያላችሁ የሥራ አስፈጻሚዎች ብቃታችሁ የሚለካው አሁን ነው። ስፖርቱን እንዴት ልጥቀመው የሚለውን ሃሳብ ያዙ፤ እንዴት ልጠቀም የሚል ራስ ወዳድነትን አርቀው መጣል አለባቸው። በሠሩት መልካም ተግባር ሃገርን በበጎ ከማስጠራት ባለፈ የሚኮሩበት ሃሳብና ተግባር ይዘው ስፖርቱን ለመምራት መዘጋጀት አለባቸው።

# ነፃ ሃሳብ

## «ከምንም ነገር በላይ በጋራ መልማት እና ሰላማችንን ማጠናከር የጋራ ዕጣችን መሆኑን አውቀን መንቀሳቀስ መቻል አለብን»

- አቶ ጌታቸው ረዳ፣
የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት

**/የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ፣ «ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና» በሚል መሪ ሀሳብ በተካሄው ሰላም የማፅናትና የዕውቅና መርሐ ግብር ላይ ያስተላለፉት መልእክት ሙሉ ቃል /**



“ከፌዴራል መንግሥት ጋር የጀመርናቸው መልካም ግንኙነቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ትልቅ ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ እምነታችን የፀና ነው። ከሁሉም አካባቢዎች የሚነሱና የሚመጡ እገዛዎችን የመጠቀም ባሻገር፤ ከምንም ነገር በላይ በጋራ መልማት፣ ሰላማችንን ማጠናከር የጋራ ዕጣችን መሆኑን አውቀን መንቀሳቀስ መቻል አለብን” ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል። የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳን ሙሉ ንግግር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

የተከበሩ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፤ የተከበሩ ሙሳ ፋቂ መሃማት፣ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር፤ የተከበሩ ቺፍ ኦሊሴንጎ አባሳንጆ፣ የአፍሪካ ኅብረት ከፍተኛ ደረጃ ፓናል ሰብሳቢ፤ የተከበሩ ኡሁሩ ኬኒያታ፣ የኬኒያ የቀድሞ ፕሬዚዳንት እና የፓናሉ አባል፤ የተከበሩ ዶክተር ሙፉዚሌ ምላንቦ፣ የደቡብ አፍሪካ የቀድሞ ምክትል ፕሬዚዳንት እና የፓናሉ አባል፤ ሁላችሁም ወንድሞች እና እህቶች፣

ከፕሪቶሪያ ስምምነት መፈረም በኋላ በርካታ መሻሻሎችን አሳይተናል። ይህንን መሻሻል ለማየት፣ ወደዚህ የደረስንበትን ርቀት ለማየት፣ የቀሩንን ለማጠናቀቅ በግልጽ እዚህ መድረክ ላይ እንደተገለጸው ጦርነት ይብቃ ማለት አንድ ነገር ሆኖ፤ ሰላማችንን ማጽናት የእንዳንዱን ሰው ጥረት የሚጠይቅ ስለሆነ ይህንኑ ለመፈተሽ ፤ ይህንኑ ለማጠናከር የሚያስችል መድረክ ስለተዘጋጀ ያዘጋጁትን የሥራ ኃላፊዎች እና የኢፌዴሪን መንግሥት በዚህ አጋጣሚ ማመስገን እፈልጋለሁ።

ላለፉት ሁለት ሦስት ዓመታት እጅግ ደም አፋሳሽ ጦርነት ውስጥ አልፈናል። ሕጻናት አልቀዋል፤ ሴቶች፣ ሁሉም አይነት ተዋጊዎች ብቻ ሳይሆኑ ውጊያ ውስጥ ያልነበሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አልቀዋል። ቅድም አንዳንድ ተናጋሪዎች ሲሉት እንደነበረው ልዩነቶቻችንን በሰለጠነ መንገድ መፍታት ሲገባን ጠመንጃ የመነቅነቅ አባዜ በርካታ መቶ ሺዎችን አስከፍሎናል ብቻ ሳይሆን ይህ ነገር ባይፈጠር ኖሮ ልንደርስበት እንችል የነበረ የእድገት ደረጃ ፣ የመረጋጋት ደረጃ ፣ የተሰሚነት ደረጃ፣ ወደ ኋላ እንዲመለስ በማድረግ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል።

በትግራይ በኩል ከፕሪቶሪያ መፈረም በኋላ ቺፍ ኦባሳንጆም እንደተናገሩት መፈረም አንድ ነገር ሆኖ ሰላሙ እንዲጸና ማድረግ እጅግ ወሳኝ ስለሆነ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በመሠራታቸው ምክንያት የትግራይ ሕዝብ አሁን እየታየ ያለውን የሰላም ተስፋ ወደ ኋላ ሊመለስ የሚችል ምንም አይነት ነገር የሚታገስ ሕዝብ አይደለም። በእያንዳንዷ ደቂቃ፤ በእያንዳንዷ ሰከንድ ሰላሙ እንዲሰፋ፤ አሁንም በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩ ችግሮች ሙሉ በሙሉ ተቀርፈው ወደ ተሟላ ኑሮው እንዲመለስ እንጂ፤ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ጥይት እንዳይተኮስ አሁን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ይዘጋ ብለን የወሰንነው ጦርነት በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ኋላ እንዲመለስ ፍጹም ፈቃደኝነት የለውም።

ስለዚህ የፕሪቶሪያ ስምምነት ብዙ ያመጣቸው ለውጦች አሉ። እንደተባለው ከፕሪቶሪያ መፈረም በኋላ የድፍረት ርምጃዎች የተወሰዱባቸው አጋጣሚዎች አሉ። በዚህ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሂደቱ እንዲፋጥን በማድረግ የወሰዷቸውን ድፍረት የተሞላባቸው ርምጃዎች በዚህ አጋጣሚ ሳላደንቅ ባልፍ ንፉግነት ነው የሚሆነው። እነዚህ ድፍረቶች አሁንም መቀጠል መቻል አለባቸው። ድፍረት በሚያንሰን ሰዓት የሚያግዙን እነዚህ ድፍረቶች ስለሆኑ። ከፕሪቶሪያ በኋላ ብዙ ለውጥ ታይቷል። የሚቀሩ ጉዳዮች አሉ።

አሁንም በጋራ ሆነን መጀመሪያ የነበረን የመተማመን መንፈስ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበር። ቀስ በቀስ ወደ ተሻለ የመተማመን መንፈስ እያሳደግነው መጥተናል። ይሄ የመተማመን መንፈስ ሌሎች አግዘውን የመጣ እንዳልሆነ በግልጽ መታወቅ መቻል አለበት። በመቀራረባችን፣ ሰላም አማራጭ የሌለው መሆኑን በመቀበላችን የመጣ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ይሄ ማለት እዚህ ያሉ ወገኖች በተደጋጋሚ የሠሩትን ጥረት ለማሳነስ ሳይሆን፤ ወደፊትም ከጎናችን ሆነው የጀመርነውን እንድናጠናቅቅ በአፍሪካዊ የወንድማማችነት መንፈስ የጀመሩትን እስከመጨረሻው እንደሚቀጥሉበት ከጎናችን እንደሚሆኑ እምነቴን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እፈልጋለሁ።

እዚህ ውስጥ የተሳተፉ ታዛቢዎች አሉ፤ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ፣ ማይክ ሃመር፣ሃና ቴተህ፣ አምባሳደር ባንኮሌ፣ ሁላችሁም በቀጣይ ሂደት ውስጥ የራሳችን የመተማመን መንፈስ ሰላምን የማጽናት ሥራ የኛና የኛ ሥራ ቢሆንም፤ የጀመርነውን እስክናጠናቅቅ ግን ወደፊትም ሀገራችን የጠፉ ማኅበረሰቦቻችንን፣ የፈራረሱ ተቋሞቻችንን ለመገንባት በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ፤ በሀገር ደረጃ ፍትሕን ለማስፈን በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁሉ ከጎናችን እንደምትሆኑ በዚህ አጋጣሚ ያለኝን እምነት ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

የትግራይ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፤ ጠመንጃ የመነቅነቅ አባዜ በፍጹም አይኖረውም። በዚህ አጋጣሚ ከትግራይ ይዤ የመጣሁት የሰላምና የፍቅር መልዕክት ብቻ ነው። አሁንም ከአራት ዓመት በላይ ትምህርት የሚባል ያላዩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች አሉን፤ ትምህርት ቤት መግባት መቻል አለባቸው። አሁንም በ100 ሺህ የሚቆጠሩ ተፈናቃዮች አሉን የኔን ወላጆች ጨምሮ መመለስ መቻል አለባቸው፤ ሥራቸውን መሥራት መቻል አለባቸው።

ሁሉንም ነገር ለሰላም በሚሆን መልኩ እናድርገው። ከጎረቤት ወንድም ሕዝቦች በተለይም ከአማራ እና ከአፋር ጋር ሊያጋጨን የሚገባ ነገር ሳይኖር ግጭት ተፈጥሮ በሁላችንም ዘንድ ታሪክ ይቅር ሊለው የማይችል ብዙ ጥፋት ተፈጽሟል። ይሄንን ነገር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተን ቋንቋችንን የሰላምና የመከባበር፣ ልዩነቶቻችንን በመከባበር፣ በመቻቻል እና በሕግ ብቻ ለመፍታት ዝግጁ ሆነን እስከሠራን ድረስ በጋራ ሀገራችንን ከመገንባት አልፈን በሁለቱም በሦስቱም ጎረቤት እህትማማች ወንድማማች ሕዝቦች መካከል ተፈጥሮ ያለውን መቃቃር የሚመስል ስሜት አስወግደን ወደ ተሻለ ደረጃ የማናደርስበት ምክንያት የለም ።

ፊት ለፊት አያቸዋለሁ ሐጂ አወል ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ ከዓመታት በኋላ ሀገር አቋራጭ አውቶብስ በአፋር በኩል አልፏል። በአፋር በኩል ማለፉ ትልቅ ነገር ነው። ሀገር አቋራጭ አውቶቡሶች ከአማራ ክልል በምንዋሰንባቸው በሁሉም አካባቢዎች፣ በሁሉም አቅጣጫዎች ማለፍ መቻል አለባቸው። ዶክተር ይልቃል ይሄ ኃላፊነት የአንተ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ኃላፊነት እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እፈልጋለሁ።

እንዳልኩት ከሚለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉን ነገሮች ይበልጣሉ። ፖለቲከኞች የሰላም ቋንቋ ማውራት መቻል አለብን። በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ መርዝን የተፉ አንደበቶች ሰላምን፣ ፍቅርን መስበክ ሲጀምሩ እንደማየት የሚያስደስት ነገር ሊኖር አይችልም። ይሄንን ካደረግን አብዛኛውን የግጭት ምክንያት የምንፈታው ይመስለኛል። የሚያቃቅሩን የሚመስሉት አሁንም በሕግ እና በሕግ ብቻ መፍታት ያሉብን በርካታ ነገሮች ያሉ ቢሆንም፤ እንዳልኩት መድፈር ነው የተሻሉ ውጤቶችን ሊያመጣልን የሚችለው ደፍረን የማይደፈሩ የሚመስሉ ሥራዎችን ሰርተን ወደፊት መቀጠል እንደምንችል ማሳየት አለብን።

አሁንም በተደጋጋሚ ታዛቢዎች ያሉት ነገር አለ፤ በተደጋጋሚ የአፍሪካ ወንድሞቻችን የፓናሉ አባላት ያሉት አለ፤ ኢትዮጵያ ከዚህ በተሻለ ሰላሟን ያጣች አገር ሳትሆን ለጎረቤት አገር ሰላም የምትደርስ አገር መሆን ይኖርባታል። ይህን ማድረግ የሚያስችል ሁላችንም አቅማችንን ማስተባበር ይጠበቅብናል።

ይህን ለማድረግ ግን በውስጥ የሚከሰቱ ችግሮቻችንን በሰለጠነ መንፈስ ለመፍታት ያለን ዝግጁነት ለአንድ ወይንም ለሌላ አካባቢ የሚተው ሳይሆን፤ ሁሉም ግጭት የሚታይባቸው አካባቢዎችን የሚመለከት መሆን መቻል አለበት። ያው በነካ እጁ ዶክተር ዐቢይ ሌሎች አካባቢዎች የሚታዩ ግጭቶች ምልክቶችንም በሆደ ሰፊነት መንገድ በድፍረት ለመፍታት እንደሚንቀሳቀስ፤ ይህን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት እኛም የበኩላችንን እንደምናደርግ በዚሁ አጋጣሚ መግለፅ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ትልቅ ደረጃ ላይ የመድረስ፣ የሕዝቦቿን ሁሉን አቅም ተጠቅማ መልሳ ለሕዝቦቿ መልሳ የምትሰጥ ሀገር የመሆን አቅማ እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህን ከፍተኛ አቅም እውን ለማድረግ የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ መቻል አለብን። አሁንም ደግሜ ደጋግሜ እንደምለው የትግራይ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፣ አንገሽግሾታል ብቻ ሳይሆን ሌሎች አካባቢዎች የሚወሰዱ ሕፃናትን ወደ ትምህርት ቤት በሰዓቱ ማድረስ መመለስ፣ማረስ ፣ማለስለስ፣ ማጨድ፣ መዝራት የሚባሉ ነገሮች ይናፍቁታል። ፈጥነን ወደ እዚህ መመለስ አለብን። ለዚህም የሁሉንም አቅም መጠቀም ያስፈልጋል። ከምንም ነገር በላይ ጠንካራ ሠራተኛ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ተመልሶ ወደ ሥራው ተሰማርቶ የሰላም ችግር ሳይሆን ምን ያህል አተረፍኩ? ምን ያህል አመረትኩ? በሚል ፉክክር ውስጥ እንዲገባ ለማስቻል የጀመርነውን ጥረት አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

ሁሉም ክልሎች የዚህ ተግባር ተሳታፊ እንደሚሆኑ እምነቴ የፀና ነው። ከፌደራል መንግሥት ጋር የጀመርናቸው መልካም ግንኙነቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ትልቅ ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ እምነታችን የፀና ነው። ከሁሉም አካባቢዎች የሚነሱና የሚመጡ እገዛዎችን የመጠቀም ጉዳይ ሳይሆን ከምንም ነገር በላይ በጋራ መልማት፣ ሰላማችንን ማጠናከር የጋራ ዕጣችን መሆኑን አውቀን መንቀሳቀስ መቻል አለብን። ይህን ለማድረግ በበኩላችን ዝግጁዎች ነን።

በመጨረሻ ማንሳት የምፈልገው ነገር ሰላም በመፈክር ብቻ እንደማይመጣ አውቃለሁ። ቢያንስ ቢያንስ ግን የሰላምን ቋንቋ መናገር መጀመር፣ ቢያንስ ቢያንስ ግን የፍቅር ቋንቋ መናገር መጀመር በዙሪያችን ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን ቅድም በሙዚቃ ድራማው ላይ እንደነበረው ከይዋጣልን መንፈስ ወጥተን በመረዳዳትና በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ ከባቢዎችን ለመፍጠር ስለሚያግዝ ሁላችንም እንደ ፖለቲካ መሪዎች ብቻ ሳይሆን እንደ ጸሐፍት፣ እንደ ተዋናይና እንደጋዜጠኞች መልካም ቋንቋን መለማመድና የየቀን ቋንቋችን የማድረግ ጥረት መጀመር አለብን የሚል እምነት አለኝ።

በዚህ አጋጣሚ በትግራይ ሕዝብና በራሴ፤ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ስም ሰላም እንዲፀና እና ጦርነት እንዲበቃ የወሰነውንና የፈረምነውን ያህል፤ መልካም መሠረት እንዲይዝና ሰላም እንዲፀና ሁላችንም የበኩላችንን ጥረት እንደምናደርግ በዚህ አጋጣሚ እምነቴን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። አክባሪ ይስጥልኝ፤ አመሰግናለሁ።

# ወቅታዊ

# «ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሰጧቸውን ጥበቃ አለአግባብ በመጠቀም ታክስ ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት ተገቢ አይደለም»

**- አቶ ዋሲሁን አባተ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ጉዳዮች አማካሪ**

ወንድወሰን ሽመልስ

**ኢትዮጵያ ዘለግ ባለው የታሪክ ምዕራፏ ግብር እየሰበሰበ አገር የሚመራ የመንግስት ሥርዓትን ስትተገብር የቆየች አገር ስለመሆኗ ይነገራል። ዛሬም የግብር አስተዳደር ስርዓቷን ከዘመኑ ጋር እንዲራመድ እና ግብር እና ታክስ መንግስት የሚያስፈልገውን ዓመታዊ ገቢ ከፍ ያለ ድርሻ እንዲሸፍን ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነች ነው። አዲስ ዘመንም ለዛሬው የወቅታዊ ገጽ ግብርን በተመለከተ እንዲሁም የግብር አስተዳደር ብሎም በኢትዮጵያ ያለውን መልካም እድልና ፈታኝ ሁኔታ ከነመፍትሄ ሃሳቡ እንዲያጋሩን ከካበተው ልምዳቸው በመነሳት ሃሳብ አስተያየታቸውን እንዲያጋሩን አቶ ዋሲሁን አባተን አነጋግረናል። አቶ ዋሲሁን አባተ፣ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሕግ፤ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በታክስ በተለይም በዓለም አቀፍ ታክስ ላይ ይዘዋል። ለ40 ዓመታት በገንዘብ ሚኒስትቴር ውስጥ ከባለሙያነት እስከ የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተርነት ባሉ የተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሰሩ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓትም በታክስ ትራንትስፎርሚሽን ጽህፈት ቤት የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ጉዳዮች አማካሪ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ግብር እና ታክስ ካለው ዓላማ አኳያ በኢትዮጵያ እንደምን የሚገለጽ ነው?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** የታክስ እና ግብር የመጀመሪያው ዓላማ ገቢ መሰብሰብ እንደመሆኑ፤ የምንፈልገውን ያህል ገቢ ሰብስበናል ባንልም ታክስ እና ኢትዮጵያ የቆየ ትስስር አላቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ እንደተጀመረ የሚወራው ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ ነው። ከዛም ወዲህ የነበሩ መንግስታት ሁሉ ታክስ ሲሰበስቡ ቆይተዋል። መንግስታት ኢትዮጵያን እንደ ኢትዮጵያ እስከዛሬ ድረስ ማስቀጠል የቻሉት በዋነኛነትም በታክስ አማካኝነት በሚሰበሰበው ገቢ ነው። አሁን ባለችበት ቁመና እንድትቀጥልም መንግስት በታክስ አማካኝነት የሰበሰበው ገቢ ትልቅ አስተዋጽዖ ነበረው፡፡

የኢንዱስትሪ መስፋፋትን በተመለከተ በተለይ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ኢንዱስትሪው በሚፈለገው መጠን እያደገ ባይሄድም፤ የውጪ ባለሃብቶችንም የአገር ውስጥ ባለሃብቶችንም በኢንዱስትሪው ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ እየተሰራ ነው። በዚህ ረገድ በተለይ የጉሙሩክ ቀረጥ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው። የቅርቡን እንኳን ያየን እንደሆነ፤ አሮጌ ተሽከርካሪዎች ወደ አገር እንዳይገቡ ለማድረግ በታክስ አማካኝነት የተወሰደው እርምጃ አሮጌ ተሽከርካሪ በጥቅል ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አቁሟል፡፡

ይሄ ደግሞ አሮጌ ተሽከርካሪዎች በአካባቢ ላይ ያደርሱ የነበረውን ችግር፤ እነዚህ አሮጌ ተሽከርካሪዎች የተሟላ ቁመና የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት የትራፊክ አደጋን በማባባስ ረገድ የነበራቸውን ውጤት፤ ለመለዋወጫ የምናወጣውን ከፍተኛ ወጪ፤ የነዳጅ ፍጆታቸው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ለነዳጅ የምናወጣውን ወጪ በመቀነስ እና በሌሎችም ምክንያቶች የተወሰደው የታክስ ፖሊሲ ርምጃ ትልቅ ጠቀሜታ አስገኝቷል። ስለዚህ አገርን እንደ አገር በማስቀጠል፤ የኢኮኖሚ ልማቱን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በማሳደግ፤ አካባቢ እና ጤና ላይ ይደርስ የነበረውን ችግር በማቃለል ረገድ ታክስ ትልቅ አስተዋጽዖ ነበረው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የታክስ ዓላማን ማስፈጸሚያ ጥሩ የሚባሉ የታክስ ሕጎች ቢኖሯትም በሚፈለገው ልክ ውጤት እንዳልተገኘባቸው ይነገራል። በዚህ ላይ የእርስዎ ሃሳብ ምንድን ነው? ሕጎቹን ከውጤታማ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ጋር እንዴት አስተሳስሮስ መራመድ ይቻላል?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** አቅም የሚገነባው በጊዜ ሂደት ነው። እስካሁን ያለውን አፈጻጸም ያየን እንደሆነ የሚያስደስት አይደለም። ሕጎች ከየትም አገር ቀርጾ ማምጣት፤ መዋስም ይቻላል። እነዚህን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አስተሳስሮ ስራ ላይ ማዋልም ይቻላል። ሕግ ማውጣት ብቻውን ግብ አይደለም። ግቦቹ ቀደም ብዬ በታክስ ዓላማ ላይ የዘረዘርኳቸው ናቸው። በመሆኑም እነዛን በማሳካት ረገድ ትልቅ ችግር አለ፡፡

የመጀመሪያው ገቢ ነው። ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ተገቢውን ሃብት በመሰብሰብ ረገድ የሚታየው ትልቅ ክፍተት ነው። ይህ አንድ ትልቅ ድክመታችን ነው። በየጊዜውም ይህንን ለማሻሻል የተለያዩ ርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው። ግን አሁንም አጥጋቢ የሆነ ውጤት ተገኝቷል ማለት አንችልም። ለምሳሌ ኮትሮባንድን በመከላከል ረገድ የተወሰነ እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም አጥጋቢ ውጤት እየታየ አይደለም። እናም እነኚህ በግብር አሰባሰብ፣ ሕገ ወጥ ንግድንና ኮትሮባንድን በመከላከል ረገድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ ሊፈቱ የሚገባቸው ተጠቃሽ ችግሮች አሉ። አንዱና ትልቁ ችግር የሰው ኃይል አቅም ነው። በመሆኑም የሰው ኃይላችንን በቁጥርም፣ በአቅምም በሚገባ ማጠናከር ያስፈልጋል። ሁለተኛው ድርጅት/አደረጃጀት ነው። ስለዚህ ተገቢ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። ሦስተኛው ህብረተሰቡ ስለ ታክስ ያለውን ንቃተ ሕሊና ማሻሻል ነው። ግብር ከፋዩም “የቄሳርን ለቄሳር” በማድረግ ኃላፊነቱን በታማኝነት መወጣት አለበት። እነኚህን እርምጃዎች መውሰድ ከተቻለ በሂደት የምንፈልገው ደረጃ ላይ እንድንደርስ ያግዛሉ ብዬ አስባለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎም እንዳነሱት አገራዊ የታክስ አስተዳደር ዋና ዋና ፈተናዎች ከሚባሉት መካከል አገራዊ የታክስ ሞራል በምን ሁኔታ የሚገለጽ ነው?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** የታክስ ንቃተ ሕሊና ስንል፣ በመጀመሪያ ሕብረተሰቡ የሚከፍለው ታክስ ለሚገኘው አገልግሎት የሚውል ነው፤ ስለዚህ እኔ ካልከፈልኩኝ የመሰረተ ልማት አቅርቦት የለም። የመንግስት አገልግሎት የለም፤ የአገር ሉዓላዊነት የለም፤ ታክስ ስከፍል ግን የእኔም የልጆቼም፣ የወደፊቱም ትውልድ ሕይወት ይለወጣል፤ ስለዚህ ታክሴን መክፈል አለብኝ የሚል ከውስጥ የመነጨ እምነት ሊኖረው ይገባል። ይሄ እምነት በሌለበት ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ህብረተሰብ በፈቃደኝነት ታክሱን የሚከፍልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡


ሁለተኛው ታክስ የማይከፍለውን ሰው መፀየፍና መቃወም አለመቻል ነው። ምክንያቱም እኔ ታክስ የምከፍል ከሆነ፣ እኔ በከፈልኩት ታክስ በተገነባ መሰረተ ልማት ታክስ ሳይከፍል የሚጠቀም ሰው እንዲኖር መፍቀድ የለብኝም። ስለዚህ ጎረቤቴ ታክስ ካልከፈለ አንተ ግብር እየከፈልክ አይደለም፤ እየተጠቀምክ ያለኸውም እኔ በከፈልኩት ታክስ በተሰራው ነው ብለን መቃወም መቻል አለብን።

ለምሳሌ በየመንደራችን የኮብልስቶን መንገድ በመዋጮ ሲሰራ፣ ያ ኮብልስቶን ተሰርቶ በቅርበት ስለምናየው እና አንድ ሰው ካላዋጣ ሥራው በተሟላ ሁኔታ እንደማይጠናቀቅ ስለምንገነዘብ እርስ በርሳችን ያላዋጣውን ሰው ዝም አንለውም። እከሌ አላዋጣም ብለን በእድርም ሆነ በሌላ ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንጠይቀዋለን። የሚፈለገው ይህንን ወደ አገር ማስፋት ነው። ሁላችንም ታክስ ካልከፈልን መንግስት ከየትም ስለማያመጣ የአገር ሰላምና ፀጥታ ሊጠበቅ አይችልም ብለን ማሰብ አለብን። ምክንያቱም በእርዳታና ብድር የለማ አገር የለም፤ ኢትዮጵያም ይህ ባህል የላትምና ህብረተሰቡ ይህንን መረዳት አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የግብር ንቃተ ሕሊናችን አነስተኛ የመሆን መገለጫ ተደርገው ከሚነሱባቸው ጉዳዮች መካከል በኢትዮጵያ ባሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን የገቢ ግብር የማይከፍሉ (ጥቂቶች እየከፈሉ መሆኑ ሳይዘነጋ) መሆናቸው ነው። በዚህ ላይ እርስዎ ምን ይላሉ? ምን የመፍትሄ ሃሳብስ ያቀርባሉ?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** በመጀመሪያ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አሉ። ስለዚህ የግብር ሕጎቻችን እነኛን የዓለምአቀፍ ስምምነቶች አክብረው መቀረጽ ስላለባቸው የተቀረጹት በዛ መልክ ነው። ለምሳሌ ማናቸውም ቀጣሪ ከተቀጣሪው ደመወዝ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት። ይህን ግዴታ ግን በዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለይም በዲፕሎማቲክ ኮሚዩኒቲው (የዲፕሎማቲክ ሂሚዩኒቲ ባላቸው) ላይ መጣል አይቻልም። ስለዚህ እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ በየሶስት ወሩ ራሱ ሄዶ ለታክስ ባለስልጣን ገቢውን አስታውቆ ግብሩን መክፈል ነው ያለበት፡፡

በዚህ ረገድ በየሶስት ወሩ ሄደው ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለታክስ ባለስልጣን አስታውቀው የገቢ ግብር የሚከፍሉ ጥቂት ሃቀኞች እንዳሉ ይታወቃል። አብዛኛው በዓለማቀፍ ድርጅቶች ውስጥ እና በዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ውስጥ የሚሰራው ሰው ግን አይከፍልም፡፡


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ይህ የሚመነጨው ደግሞ አንድም ከስስት ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ከኢትዮጵያ የተሻለ ደመወዝ ስለሚያገኙ ከዛ ላይ ቀንሰው የሚከፍሉት ያሳሳቸዋል። ስለዚህም ከህሊና ጸጸት ጋር እየታገሉም ቢሆን የሞራል ግዴታቸውን እንዳይወጡ ያደርጋቸዋል። እናም ስለ አገር ሰላም፣ ስለ መሰረተ ልማት ሲወራ፣ ስለ ሌሎችም የልማት ስራዎች በሚወራበት ጊዜ በእነዚህ ከመጠቀም የዘለለ ምንም አስተዋጽኦ የላቸውም፤ አያደርጉምም። ስለዚህ የዚህ አገር ዜጋ ነኝ፤ ይህ አገር እንዲህ አይነት አገልግሎት ሊያሟላ ይገባል፤ እንዲህ አይነቱን አገልግሎት ማስፋፋት አለበት ብለው መናገርም አይችሉም። ምክንያቱም እነሱ ግዴታቸውን ሳይወጡ ይህን አይነቱን ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም። ከዛ አንጻር የሞራል ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

ሁለተኛው የሕግ ግዴታ አለባቸው። እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን የታክሱ ባለስልጣን የደረሰባቸው እንደሆነ ሃብት ንብረታቸው ተሸጦ እንደሚከፈል ግልጽ ነው። ይሄ ደግሞ ለራሳቸውም ትልቅ አደጋ ነው፤ ለቤተሰባቸውም ጥለው የሚሄዱት ስጋት በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም ታክሱ እየተጠራቀመ ሲሄድ እየተደመረ እየተደመረ መጨረሻ ላይ ከሚያገኙት ገቢ ላይ ሊከፍሉት አይችሉም። ስለዚህ የሚከፈለው ንብረታቸው ተሸጦ ነው። መንግስት እነደዛ አይነት ጠንካራ ርምጃ ወደ መውሰድ የገባ እለት ቤተሰባቸው ይበተናል፤ ያፈሩት ሃብት ተሸጦ ለታክስ እዳ የሚውልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በመሆኑም የሕግ ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው። ምክንያቱም ዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ (ለምሳሌ፣ የቬና ስምምነት እና ሌሎችም የኢትዮጵያ መንግስት የፈረማቸው) የሰጧቸውን ጥበቃ አለአግባብ በመጠቀም ታክስ ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ይህንን አውቀው የመክፈል እንቅስቃሴ መጀመር አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ሰዎች ወደ ግብር ስርዓቱ እንዲገቡ ምን መሰራት አለበት?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** በዚህ ረገድ ትልቁ ድክመት ያለው በታክስ ባለስልጣኑ በኩል ነው። እርግጥ የታክስ ባለስልጣኑ፣ ሰራተኞቹ የት መስሪያ ቤት ነው የሚሰሩት፤ ምን ያህል ደመወዝ ነው የሚያገኙት፤ የት ነው የሚኖሩት የሚለው መረጃ ከሌለው ይህንን ታክስ መሰብሰብ አይችልም። በዚህ ረገድ በቬና ስምምነት መሰረት ኤምባሲዎቹን ኑ! መረጃ ስጡን ብሎ ማስገደድ ስለማይቻል መረጃው ላይገኝ ይችላል። አንዳንዶች ግን ተባባሪ ሆነው የሰራተኞቻቸውን ስም ዝርዝር እና የደመወዛቸውን ልክ ሊገልጹልን ይችላሉ። ከዛ አልፎ ግን ማስገደድ አይቻልም፡፡

ስለዚህ እንደ እኔ ይህንን መረጃ ለማግኘት የሚኖረን አማራጭና ቀላል የሚሆነው መንገድ ቀበሌዎችን መጠቀም ነው። በየአከባቢው ያሉ የቀበሌ አስተዳደሮች በቀበሌያቸው ውስጥ የሚኖረው ነዋሪ የቱ የመንግስት ሰራተኛ ነው፤ የቱ የዓለም አቀፍ ድርጅት ሰራተኛ ነው፤ የቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሰራተኛ ነው፤ የቱ ስራ የሌለው ነው የሚለውን በሪከርዳቸው ላይ ይኖራቸዋል፡፡

ከዛ ተነስተውም እየሄዱ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰዎችን ታክስ የመክፈል ግዴታህን ተወጥተሃል ወይ ብሎ መጠየቅ፤ እንዲከፍል ማነሳሳት፤ እንቢ ካለ ደግሞ ዝርዝሩን ለታክስ ባለስልጣን ሰጥተው የታክሱ ባለስልጣን እነዚህን ሰዎች በቀበሌው አማካኝነት የታክስ ማስታወቂያ እንዲደርሳቸው ማድረግና ታክሱን መሰብሰብ ይገባዋል። ይሄን ባለማድረጋችን እኔ እስከማውቀው ድረስ ሃያ እና ሰላሳ ዓመት ለሚሆን ጊዜ ከእነዚህ ሰዎች ታክስ አልተሰበሰበም ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ከአንቀጽ 96 እስከ 100 ባሉት ድንጋጌዎች ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣን ለፌዴራል እና ለክልል መንግስታት ከፋፍሎ ይሰጣል። ሆኖም በአተገባበር ሂደት በየደረጃው ክፍተት እንዳለ ይነገራል። በዚህ ላይ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** እንደተባለው ሕገ መንግስቱ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣንን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዟል። ሕጎችም እየወጡ ያሉት በዛ መሰረት ነው። በዚህ ረገድ የሚታይ ችግር የለም። ነገር ግን የፌዴራል አደረጃጀት ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ሁሉ፤አንዳንድ ጊዜ በፌዴራልና በክልሎች፣ በክልልና በክልል መካከል የታክስ

# ወቅታዊ

ስልጣን አተገባበር ላይ ችግር መኖሩ አይቀርም። ሆኖም እነዚህን ችግሮች መፍቻ ስርዓት ሕገ መንግስቱ ራሱ አለው። ስለዚህ አንዳንድ አይነት ታክሶች ላይ በክልሎች መካከል መወዳደር፤ ይህ ታክስ የእኔ ነው፣ ወይም እዚህ ላይ እኔ እሰበስባለው የሚል ከሕገ መንግስቱ ጋር ትንሽ የማይሄዱ ነገሮች አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡

እነኚህን ስርዓት ማስያዝ ይቻላል። ምክንያቱም ሕገ መንግስቱ እንዲህ አይነት ችግሮች ሲያጋጥሙ ለእነዛ ስርዓት አስቀምጧል። ይህም ስርዓት መጀመሪያ መነጋገር ነው፤ ካልተቻለ ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት መውሰድ ነው። ፌዴሬሽን ምክር ቤትም በታክስ ረገድ በክልሎች መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ካለ መፍታት ይችላል። በፌዴራልና በክልልም መካከል ካለ በተመሳሳይ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በፊትም መሰል ጉዳዮችን በዚህ መልኩ ፈትተናል። ለምሳሌ የኪራይ ገቢ ግብርን በተመለከተ በክልሎችና በፌዴራል መንግስት መካከል አተገባበር ላይ ችግር ነበር። ይሄ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ በጥናት ተፈትቷል። አሁን በዛ ረገድ ችግር የለም። ሌሎችም ችግሮች በዚሁ መልክ እየተፈቱ ሊሄዱ የሚችሉ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የታክስ ፍትሃዊነትን በተመለከተ፤ ለምሳሌ አርሶና አርብቶ አደሩ አካባቢ አርሶ ከሚያገኘው አንጻር ግብር አከፋፈሉ ፍትሃዊነት የጎደለው እንደሆነ ይነሳል። በዚህ ላይ የእርስዎ ምልከታና የመፍትሄ ሃሳብ ምንድን ነው?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በዋነኛነት ሁለት አይነት ታክስ እንዲከፍሉ ይጠበቃል። አንዱ በይዞታቸው ስር ባለው መሬት የመጠቀም መብት የመጠቀሚያ ክፍያ ሲሆን፣ ሁለተኛው በዛ መሬት አምርተው ለሚያገኙት ገቢ የሚከፍሉት ግብር ነው። እነኚህ ሁለቱም ላይ ታክስና ግብር የመሰብሰብ ስልጣን ሕገ-መንግስቱ ለክልሎች ነው የሚሰጠው። ሆኖም ከድሮም ጀምሮ ሰፊ ከሆነው አርሶና አርብቶ አደር የእያንዳንዱን ሰው ገቢ አውቆ ታክሱን መሰብሰብ ቀላል አይደለም። በዚህ ረገድ የነበሩ ውጣ ውረዶችንም አስታውሳለሁ፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል ርምጃ ተወስዷል። የተወሰደው ርምጃ ግን ፍትሃዊነትን አጠፋ። ለምን ቢባል የእርሻ ስራ ገቢ ግብሩ በገቢ ላይ ተመስርቶ የሚከፈል ነው እንጂ በመሬት ስፋት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል አይደለም። ስለዚህ አንዳንድ ሰው በጣም ለምና ሰፊ መሬት ይዞ ትንሽ ታክስ ይከፍላል። አንዳንድ ሰው ደግሞ ምርት የማይሰጥ ትልቅ መሬት ይዞ በጣም ትልቅ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል። ምክንያቱም የሚታየው ምርታማነቱ ሳይሆን የያዘው መሬት ስፋት ስለሆነ ነው። የታክሱ መርህ ግን በገቢ ላይ እስከሆነ ድረስ መሆን ያለበት የይዞታ ስፋትን መሰረት አድርጎ አይደለም፤ ይዞታውም ገቢውን ሊናገር አይችልም። ገቢውን ሊናገር የሚችለው ከመሬቱ የተመረተው ምርት ስንት ነው፤ ስንት ዋጋስ አለው የሚለው ነው፡፡

በዚህ ረገድ ፍትሃዊነትን የሚያጠፉ አንዳንድ ችግሮች አሉ። ትልቁ ደግሞ የታክስ መርህ ፍትሃዊነት ነው፤ ስለዚህ ይህን የግብር ፍትሃዊነት የሚያጠፉ ጉዳዮች በሂደት የፌዴራል መንግስቱም ጥናት አድርጎና ከክልሎችም ጋር ተጋግዘን መፍታት ይኖርብናል። በዓመት 200 እና 300 ብር ከዛም በታች ግብር በዓመት እየከፈሉ የሚኖሩ ትልልቅ ገቢ ያላቸው አርሶ አደሮች አሉ፤ በተቃራኒው ደግሞ አነስተኛ ገቢ ያለው ከዛ በላይ ግብር እንዲከፍል ይጠየቃል። ስለዚህ ይህንን ፍትሃዊ ያልሆነ ነገር ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የዜጎችን ጤንነት ከአደጋ ለመከላከል ሲባል በቅንጦትና በሰው ልጅ ጤና ላይ ጉዳት በሚያደርሱ ምርቶች የተጣለው ኤክሳይዝ ታክስ በታለመለት ልክ ተግባራዊ ተደርጓል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** ኤክሳይዝ ታክሱ ብቻውን ህብረተሰቡ በእነዚህ ምርቶች እንዳይጠቀም ሊያደርግ አይችልም። ሌሎችም ተዛማጅ የሆኑ ይሄንን ምርት ወደ አገር እንዳይገባም ሆነ እንዳይመረት መከላከል የሚያስችሉ ርምጃዎች አብረው መወሰድ አለባቸው። ኤክሳይዝ ታክሱንም በምንጥልበት ጊዜ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መሆን አለበት። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከጎሮቤቶቿ ጋር ሰፊ ድንበር ያላት እንደመሆኑ ይሄንን በሙሉ በሰው አጥሮ መጠበቅ አይቻልም። ኮትሮባንድን በመከላከል ረገድ የመንግስትም የህብረተሰቡም ድጋፍ ሊታከልበት ይገባል። በተለይ ለጤና ጉዳት የሚያስከትሉ እንደ ሲጋራና የአልኮል መጠጥ አይነት ምርቶች በአብዛኛው በኮትሮባንድ መልኩ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ በመሆኑ፤ እነዚህን መከላከል ካልቻልን የህብረተሰቡን ጤና መጠበቅ አይቻልም፡፡

ስለዚህ የህብረተሰቡን ጤና በኤክሳይዝ ታክስ አማካኝነት መጠበቅ የሚቻለው የእነዚህን ዋጋ በማስወደድ ነው። ነገር ግን እዚህ ታክስ ጥሎ የመጠጥና የሲጋራ ዋጋ እንዲወደድ ሲደረግ፤ በሌላ መልኩ በኮትሮባንድ ገብቶ አገር ውስጥ በርካሽ የሚሸጥ ከሆነ የአገር ውስጡን ኢንዱስትሪ ከመግደል በስተቀረ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አይቻልም። ስለዚህ ሚዛናዊ መሆን ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ ደግሞ ኮንትሮባንዱን የመቆጣጠር አቅማችን እየተጠናከረ በሄደ ቁጥር ለሲጋራውም ለአልኮል መጠጡም ሌላ ምንጭ ስለሌለ አገር ውስጥ ያለውን በማስወደድ ሰው እንዳይጠቀም ማድረግ ይቻላል። በዚህ ረገድ ኤክሳይዝ ታክስ ከተጀመረ ጀምሮ ትምባሆና መጠጥ ላይ ያለ ቢሆንም የኮንትሮባንድ ንግዱ የሚፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ አድርጎታል። ይህ ችግር የእኛ አገር ችግር ብቻ አይደለም። አሜሪካንን ጨምሮ የሁሉም አገር ችግር ነው። እናም ይህንን በቀላሉ ሙሉ ለሙሉ ማጣፋት ባይቻልም አሁን ተንሰራፍቶ ያለውን ነገር ደረጃ በደረጃ እየቀነስን ሄደን፤ ኤክሳይዝ ታክስ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማድረግ እንችላለን። ከዛ ውጪ ግን ኮንትሮባንዱ እስካልቆመ ድረስ ኤክሳይዝ ታክሱ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ስራ ሲያግዝ የሚችለው የጉምሩክ ሕጉና አተገባበሩ የወጪና ገቢ ንግድን ከማሳለጥና ፍሰታቸውን ከመቆጣጠር ባለፈ ኮትሮባንድን በመቆጣጠር ረገድ ሚናው እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** ሕጉ አለ፤ ትልቁ ችግር ሕጉ ሳይሆን ኮትሮባንድን በመከላከል ረገድ ሚና ያላቸው የተለያዩ አካላት አሉ። አንደኛው የጸጥታ ኃይሉ ነው። የፀጥታ ኃይሉ የአገርን ድንበር በሚጠብቅበት ጊዜ በተመሳሳይ የአገርን ድንበር አልፈው የሚገቡ የኮትሮባንድ ምርቶችን በመከላከል ረገድ አስተዋጽዖ ማድረግ ይኖርበታል። የክልል መንግስታትና የጸጥታ አካላትም በየአካባቢያቸው ያለውን በመቆጣጠር ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው። በመሆኑም የፌዴራል የጸጥታ አካላት፣ ክልሎችና ጉሙሩክ ኮሚሽን በተቀናጀ ሁኔታ ስራቸውን መስራት ካልቻሉ በስተቀር ኮንትሮባንድን መዋጋት በጣም አደገኛ ነው፡፡

ምክንያቱም በሕጉ በግልጽ እንደተመላከተው አንድ እቃ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ ከገባ ኮንትሮባንድ ነው፤ ኮንትሮባንድ ደግሞ ይወረሳል። እቃውን ይዞ የተገኘውም ሰው በወንጀል ይቀጣል። ይህንን ለማስፈጸም ግን እነኚህ አካላት በተደራጀ ሁኔታ ስራቸውን መስራት አለባቸው። አንዳንዴ የዘመቻ አይነት ይሆንና አንድ ሰሞን በጣም ጠንከር ብለን ኮንትሮባንድን እንከላከላለን፤ አንድ ሰሞን ደግሞ ይቀዛቀዛል፤ ይህ መሆን የለበትም፡፡

ለኮንትሮባንዲስቱ ስጋት ካልሆንን ድረስ ኮንትሮባንዲስቱ አይተውም፡፡እናም ኮንትሮባንዲስቱ በቃ አምልጬ ላስገባ አልችልም፤ ስለዚህ ቢዝነሴን መተው አለብኝ በሚያስብለው ደረጃ ስጋት መሆን አለብን። አሁን ላይ በጦር መሳሪያ ጭምር በመታገዝ የጉምሩክ ፖሊሶችንና የጉሙሩክ ሰራተኞችን በመግደል ነው ኮንትሮባንዲስቶቹ ንግዳቸውን እያስፋፉ ያሉት። እዛ ድረስ የደረሱት በኮንትሮባንድ ንግድ የሚያገኙት ጥቅም በጣም ትልቅ ስለሆነ፤ ከኪሳራው ጥቅሙ ስለሚበልጥባቸው ነው። ስለዚህ መንግስት ይህ ጥቅም የማይገኝ መሆኑን፤ ስጋቱ እንደሚበልጥ ማሳየት ከቻለ ኮንትሮባንዱን መከላከል እንችላለን። የመያዝና የመወረስ እድሉ ከፍተኛ ከሆነ ኮንትሮባንዱ እየቀነሰ ይሄዳል። ይህ በሌለበት ሁኔታ ግን ችግር ውስጥ ነው የሚከትተን፡፡

ሊታወቅ የሚገባው ዛሬ ላይ የኮንትሮባንድ ንግድ የኢኮኖሚ ጥያቄ ብቻ አይደለም። የአገር ሉዓላዊነት ጥያቄ ጭምር ነው። ምክንያቱም በዚህ ኮንትሮባንድ ንግድ ውስጥ የሚሰማሩ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ የአገርን ሰላም ለመበጥበጥ ጭምር ነው የሚውለው። ስለዚህ የኮትሮባንድ ንግድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በሌሎች አገራት እንደሚታየውም ኮትሮባንድ አገሮችን ለብዙ ችግር እያጋለጠ ነውና ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ፤ ህብረተሰቡም ተባባሪ ሊሆን ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ድሃውን ህብረተሰብ ለመደገፍ ሲባል የተጨማሪ እሴት ታክስና ሌሳም የተነሳሳቸው ዘርፎች ምን ያህል ውጤታማ ሆነዋል?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** የመሰረታዊ የምግብ አቅርቦቶች ዋጋ በጣም በናረበት ጊዜ መንግስት ዋጋ ለማረጋጋት እንደ መፍትሄ አድርጎ የወሰደው የተጨማሪ እሴት ታክስን ማንሳት ነው። ይህም 15 በመቶው ቢነሳ የሸቀጦች ዋጋ ይቀንሳል በሚል ነው። በዚህም እንደተጀመረ አካባቢው ጥሩ ውጤት ተገኝቶ፤ በተወሰነ ደረጃ ቢቀንስም እንደገና ተመልሶ ወደላይ ወጥቷል። በዚህ መልኩ ወደላይ የወጣውና ማበረታቻውን ትርጉም የለሽ ያደረገው ምንድነው የሚለውን በብዙ መንገድ ማየት ያስፈልጋል፡፡

አንዱ የሚመስለኝ፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ባልተሟላበት ሁኔታ ሰዎች አነዚህን ምርቶች ለመግዛት የሚያወጡት ወጪ ከፍተኛ ስለሚሆን ያንን መሰረት አድርገው ዋጋቸውን አንረው ሊሆን ይችላል። ሌሎች የሎጀስቲክስና መሰል ችግሮችንም መጥቀስ ይቻላል። ዋናው ነገር ግን ታክስን በማንሳት መንግስት የወሰዳቸው የፖሊሲ ርምጃዎች የተፈለገውን ያህል ውጤት አስገኝተዋል ለማለት አይቻልም። ከዚህ ያጣነው ገቢ ደግሞ በጣም ትልቅ ገንዘብ ነው። ምክንያቱ ምንድን ነው የሚለው ግን ዝርዝር ጥናት ይጠይቃል።

በዚህ ድጋፍ በዘይት፣ ስኳርና ሌሎችም ላይ ቫትን ስናነሳ ድሃው ብቻ አይደለም የሚጠቀመው። ከታክሱ መነሳት ተጠቃሚ የሆነው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ነው። ስለዚህ ይሄን ከምናደርግ 15 በመቶውን ታክስ ሰብስበን ድሃውን በቀጥታ የምንጠቅምበት ሌላ መንገድ ብንፈልግ ይሻላል ወይ የሚለው በጥናት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው ነው። ግን አሁን እንደምናየው የምርቶቹ ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ ነው፤ ስለዚህ ዋጋ በማረጋጋት ረገድ ታክሱ የሚፈለገውን ውጤት አስገኝቷል ወይ የሚለውን ለመናገር ያስቸግራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን እስካሁን ለምን ማጥናት እና መለየት አልተቻለም? ተጠንቶ ከሆነስ ምን ታጣ? ምንስ ተገኘ?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** እስከዛሬ ባልነበረ ሁኔታ በቅርቡ ሐምሌ ወር ላይ የወጣው የታክስ ማበረታቻ አዋጅ በገንዘብ ሚኒስቴር ላይ እና ማበረታቻ በሚሰጡ ሌሎችም የመንግስት አካላት ላይ ግዴታን ጥሏል። በአዋጁ የተቀመጠው ግዴታም፣ አንደኛ እያንዳንዱ ታክስ ቢሰበሰብ ኖሮ ስንት ብር እናገኝ ነበር፤ ባለመሰብሰቡ ስንት አጣን? የሚለውን መለየት ነው። ሁለተኛው ይሄንን ገቢ በማጣታችን ምን ጥቅም ተገኘ? የሚለውን መገምገም ነው። ለምሳሌ ለኢንቨስትመንት በሚሰጠው ማበረታቻ ምክንያት ለስንት ሰው የስራ እድል ተፈጠረ? የኢኮኖሚው እድገት ላይ ምን ያህል አስተዋጽዖ አደረገ? የሚሉትን የመለየትና መገምገም ነው፡፡

ለምሳሌ አስር ቢሊዮን ብር አጥቼ ከሆነ፤ አስር ቢሊዮን የሚሆን ጥቅም ሕዝቡ አግኝቷል ወይ? የሚለውን በየዓመቱ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር ለፓርላማው የማቅረብ ግዴታ ተጥሎበታል። ስለዚህ ያለፉት ስድስት ወራት ተሰርቷል። መጠኑን ልገልጽልህ ባልችልም፤ ዳታው ከጉምሩክም፣ ከሌሎችም አካላት ተሰብስቦ ምን ያህል ገቢ እንዳጣን ታውቋል። አሁን የሚቀረው ስራ ይሄን በማጣታችን ምክንያት ምን ተጠቀምን? ይሄንን ገቢ ብንሰበስብ ኖሮ ትምህርት ቤት እንሰራበት ነበር፤ ጤና ጣቢያ እንሰራበት ነበርን? ይሄንን ገቢ በማጣታችን ህብረተሰቡ በእርግጥ ዋጋው የቀነሰ ምርት አገኘ? ህብረተሰቡ የስራ እድል አገኘ? ኢንዱስትሪው የመስፋፋት እድል አገኘ/ተስፋፋ? የሚሉትን የመገምገም ስራ ነው፡፡

ይሄ ስራ ሌሎች በኢኮኖሚው ላይ ከፍ ያለ ድርሻ ባላቸው ግብርናን መሰል ዘርፎችም የሚታይ ነው። ለምሳሌ ለግብርናው የሚውሉ ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎችም ግብዓቶች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ አድርገናል። ስለዚህ በዚህ ስንት ብር ታጣ? የሚለው ተጣርቷል። የቀረው ስራ እነዚህ ትራክተሮች፣ ማሽነሪዎችና ሌሎችም ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የአገራችን አርሶ አደር እነዚህን ተጠቅሞ ምርታማነቱን በምን ያህል ጨመረ? የሚሉትና መሰል የውጤታማነት ግምገማ ስራ ከግብርና ሚኒስቴርና ባለድርሻዎች ጋር ማከናወን ነው፡፡

ይህን መገምገም ደግሞ በሕጉ ላይ በግዴታነት የተቀመጠ ስለሆነ ይህ ተገምግሞና ሪፖርቱ ተጠናክሮ ለፓርላማው ይቀርባል። ሕዝቡም እንዲያውቀው ይደረጋል። ምክንያቱም ይሄ ልክ እንደ በጀት ስለሆነ በሦስት ተከፍሎ ነው የተሰራው። የመጀመሪያው ከመሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ስንት ታጣ የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ለኤምባሲዎችና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ከሚገባው ከቀረጥ ነጻ ሸቀጥ ምን ያህል ገንዘብ ታጣ፤ እንዲሁም ሶስተኛው ለኢንቨስተሮች የካፒታል እቃዎች ከቀረጥ ነጻ በማስባት ሂደት ምን ያህል ታጣ የሚሉትን የሚመለከት መረጃ ተዘጋጅቷል። ምናልባትም በቅርቡ ይፋ ይደረጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የተደራራቢ ግብር ነጻ ስምምነትን ከአገራት ጋር መፈራረሟ ይታወቃል። የዚህ ዓላማው ምንድን ነው? ከተፈራረመቻቸው ስምምነቶችስ ምን ጥቅም አገኘች?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** የተደራራቢ ግብር ነጻ ስምምነት ዋና ዓላማው ኢንቨስትመንትን መሳብ ነው። አንድ ውጪ አገር ያለ ሰው/ባለሃብት ወደ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ሲመጣ ከሚያስባቸው ነገሮች አንዱ የታክስ ወጪ ነው። ምን ያህል ታክስ እከፍላለሁ? ምን ያህልስ ብር ይቀረኛል? ስንት ብር ይዤ ወደ አገሬ እመለሳለሁ? የሚለውን ነው የሚስበው። ስለዚህ ተደራራቢ ግብር መክፈል ካለ(አገሩም እዚህም ግብር የሚከፍል ከሆነ) ወደ አገሩ ይዞ የሚመለሰው ገንዘብ ላይኖረው ስለሚችል ወደ ሌላ አገር ሄዶ ለመስራት አይፈልግም። ስለዚህ የተደራራቢ ግብር ነጻ ስምምነት ዋናው አላማ ተደራራቢ ታክስን በማስቀረት ሰዎች/ባለሃብቶች ገንዘባቸውን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ማድረግ፤ እዚህ ሰርተውም ራሳቸውን፣ አገርን እና ዜጎችን እንዲጠቅሙ ማድረግ ነው፡፡

ሁለተኛው የታክስ ማጭበርበርን፣ በተለይ ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ ኩባንያዎች የሚፈጸሙትን በርካታ የታክስ ማጭበርበሮች መከላከል የሚያስችል ስርዓትን ለመዘርጋትና በመግባባት ውስጥ አለመግባባቶችን ለማስወገድ ነው።

በዚህ ረገድ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ፓርላማም ሆነ፣ ስምምነት በተደረሰበት አገር ፓርላማ ጸድቆ የማጽደቂያ ስምምነት የተለዋወጥንባቸው 23 የሚሆኑ ስምምነቶች አሉ። ከእነኚህ ውስጥ በጣም ጥቂቶች ናቸው ለተግባር የበቁት። ምክንያቱም ከእነኚህ አገራት ባለሃብት ካልመጣ ከስምምነቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ የለም። ይህ ከተደራራቢ ግብር ነጻ የመሆን ስምምነት ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነው። ለምሳሌ፣ የኢንቨስትመንት የእፎይታ ጊዜ ማበረታቻን ትርጉም የሚኖረውና ባለሃብት የሚስበው ይሄ ስምምነት ሲኖርና ተግባራዊ ሲሆን ነው፡፡

ለምሳሌ የመጀመሪያውን የተደራራቢ ግብር ነጻ ስምምነት የተፈራረምነው ከ20 ዓመት በፊት ከጣሊያን ጋር ነው። ስለዚህ ከጣሊያን የመጡ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እና ኢንቨስተሮች የዚህ ተጠቃሚ ሆነዋል። እዚህ በግብር እፎይታ ምክንያት ያልከፈሉትን ግብር፣ ጣሊያን አገር እንደተከፈለ ግብር ሆኖ ተደራራቢ ግብር እንዳይከፍሉ ተደርጎላቸዋል። በስምምነቱ የተወሰኑ ሌሎችም የታክስ ማስከፈያ ምጣኔዎችም ተጠቃሚ ሆነዋል። ከቻይናም ጋር መሰል ስምምነት የተፈጸመ ሲሆን፣ ቻይናውያን ባለሃብቶች የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል። ከኔዘርላንድስ የመጡ ኩባንያዎችም ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በሌላ በኩል ባለሃብቶች ይመጣሉ ብለን ስምምነቱን ተፈራርመን፣ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ከእነዚህ አገሮች ባለሃብቶች ያልመጡባቸው አሉ። እነዚህም ባለሃብቶቹ በሚመጡበት ጊዜ በጋራ ተጠቃሚ እንሆናለን ብለን እናስባለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አጠቃላይ ውጤታማ የግብር እና ታክስ ሥርዓትን ከመዘርጋት አንጻር በቀጣይ ምን ሊሰራ ይገባል ይላሉ?**

**አቶ ዋሲሁን፡-** ውጤታማ የግብር ስርዓት እውን እንዲሆን የሁሉንም ጥረት ይጠይቃል። ለምሳሌ በመንግስት በኩል የተጠናከረ የታክስ አስተዳደር ባለስልጣን እንዲኖረን ማድረግ (በፌዴራልም፣ በክልልም ደረጃ) ትልቁ ስራው መሆን አለበት። እነዚህ የታክስ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች ደግሞ የሚፈሩም፣ የሚወደዱም መሆን አለባቸው። አንደኛ ግብር ከፋዩ፣ የታክስ አስተዳደሩ ባለስልጣን ላመልጠው የምችለው አይደለም፤ ይደርስብኛል፤ ከደረሰብኝ ደግሞ በእኔም በቤተሰቤም ሃብት ላይ ጉዳት ይደርስብኛል፤ ችግር ውስጥ እገባለሁ ብሎ መፍራት አለበት። ሁለተኛ መስሪያ ቤቱ ራሱ የሰበሰበውን ገንዘብ ለተገቢው የልማት ስራ የሚያውል መሆኑ በደንበኛው ዘንድ የታመነ መሆን፤ ስሄድም በደስታ ተቀብሎ በጥሩ ሁኔታ የሚያስተናግደኝ ነው ብሎ የሚያስበውና የሚወድደው ተቋም መሆን አለበት፡፡

ይህንን ለማድረግ ደግሞ መጀመሪያ ሰራተኛውን በበቂ ሁኔታ ማሰልጠን ያስፈልጋል። ሰራተኛውም ስለ ታክስ ሕጎች በሚገባ የሚያውቅ መሆን አለበት። ግብር ከፋዩን በማስተማርና በፍቅር ግዴታውን ፈቅዶ እንዲወጣ ማድረግ የሚያስችል ሰራተኛ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡

እንደ ሰራተኛው ሁሉ አደረጃጀቱም በሚገባ መታየት አለበት። በተለይ ቴክኖሎጂን በመተግበር ረገድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ቴክኖሎጂ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው። ስራን ያቀላጥፋል፤ ግልጽነትንና መተማመንን ያሰፍናል፤ የስነምግባር ችግርን ያቃልላል፡፡

አሁን እንደሚታየው ከአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (ጂ.ዲ.ፒ) እና የሚሰበሰበው ታክስ መካከል ያለው ግንኙነት ባለፉት ዓመታት እየቀነሰ ነው። ይህ ማለት ህብረተሰቡ የግብር ግዴታውን በተገቢው መንገድ እየተወጣ አይደለም። መንግስትም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ተገቢውን ድርሻ እያገኘ አይደለም። በዛ ምክንያት የመንግስት አቅም እየደከመ እና የመሰረተ ልማት ስራ እየቀነሰ ይሄዳል ማለት ነው። በመሆኑም በሕብረተሰቡ በኩል፣ በመጀመሪያ ግብር የምከፍለው መንግስት ለሚሰራልኝ መሰረተ ልማት ስራዎች ነው፤ ቅሬታ የማሰማባቸውም የመሰረተ ልማት ጥያቄዎቼ የሚመለሱት ግብር በታማኝነት ስከፍል ነው፤ ስለዚህ የበኩሌን መወጣት አለብኝ ብሎ ማመን አለበት፡፡

በመሆኑም መንግስትም የራሱን ድርሻ፤ ህብረተሰቡም የራሱን ድርሻ ከተወጣ ታክሱ ተሰብስቦ የአገራችንን ልማት ወደፊት ማራመድ እንችላለን። ይህንን የምናደርገው ደግሞ ለራሳችን፣ ለልጆቻችን ብሎም ለወገናችን ብለን ነው። መንግስትም ለዚህ የበጀት ግልጸኝነትን ማስፈን፤ ስራዎችንም መግለጽ አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ሆነው ሃሳብዎን ስላጋሩን ከልብ እናመሰግናለሁ!**

**አቶ ዋሲሁን፡-** እኔም እድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ!

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ሰላምን ማፅናት - ለኢንቨስትመንት እድገት

**አንተነህ ቸሬ**



የሰላም ስምምነቱ ሀገሪቱ ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ በሚል የገነባቻቸው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ይበልጥ እንዲነቃቁ ያስችላል

ሰላምና መረጋጋት በሌለበት ሀገር የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና እድገት ፈፅሞ የሚታሰብ አይደለም። የኢንቨስትመንት ሥራ ሰላም ይፈልጋል። ግጭትና ጦርነት ያለባቸው አካባቢዎች አዳዲስ የኢንቨስትመንት እድሎችን ማግኘት ይቅርና፣ በአካባቢዎቹ ያሉ የኢንቨስትመንት መዳረሻዎችንና ተቋማትን ይዘው መቆየት አይችሉም፤ ባሉበት የመቀጠል እድላቸውም እጅግ ዝቅተኛ ይሆናል። እንኳን በተግባር የሚታይ የሰላም እጦት፣ ተጨባጭ ማስረጃ የሌለው ወሬም ኢንቨስትመንትን ያስደነግጣል። ለዚህም ነው ‹ሰላም የኢንቨስትመንት መተንፈሻ ነው› የሚባለው።

«ዴቨሎፕመንት ኢኒሼቲቭስ» (Development Initiatives) የተባለ የጥናት ተቋም ይፋ ባደረገው ሪፖርቱ፤ በሰላምና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ግንኙነት የዓለም አቀፍ ልማትና የምጣኔ ሀብት እድገት ወሳኝ የትኩረት ነጥብ እንደሆነ አመላክቷል። በግጭትና ጦርነት ውስጥ የተዘፈቁ ሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፋቸው የተዳከመ መሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተያዙ የልማት እቅዶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይሳኩ እክል መፍጠሩ እንደማይቀርም ስጋቱን ገልጿል።

ሰላም ከኢንቨስትመንት ጋር ምን ዓይነት ቁርኝት እንዳለው ያለፉት ጥቂት ዓመታት ኢትዮጵያ ጥሩ ምስክር መሆን ከሚችሉ ሀገራት መካከል እንደምትመደብ አያጠራጥርም። በእነዚህ ዓመታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ አለመረጋጋቶች፣ በተለይም የሰሜኑ ጦርነት፣ በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ ጉዳት አድርሰዋል። በእነዚህ አለመረጋጋቶች ምክንያት ውድመትና ዝርፊያ የተፈፀመባቸው የኢንቨስትመንት ተቋማት የደረሰባቸው ጉዳት የሚዘነጋ አይደለም። ይህ ሁኔታም ሠራተኞች ከሥራ እንዲፈናቀሉ፣ ምርትና አገልግሎት እንዲቀንስ እንዲሁም ኢንቨስትመንት እንዲዳከም በማድረግ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል።

ባለፈው ዓመት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ክስተቶች ለኢንቨስትመቱ ዘርፍ መሰናክል እንደነበሩ በተደጋጋሚ ተገልጿል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም በ2104 ዓ.ም የበጀት ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ ይፋ ባደረገው መረጃ፣ ከጦርነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የኢትዮጵያ ከአጎዋ (AGOA) መታገድ እና የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጫና በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግዳሮቶች መካከል ተጠቃሽ እንደነበሩ መግለፁ ይታወሳል።

ሰላምና መረጋጋት ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተለይ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ በኢንቨስትመንት ላይ ተሠማርተው የነበሩ ትልልቅ አምራች ድርጅቶችን ትልቅ ጫና ውስጥ አስገብቷቸዋል። አለመረጋጋቱን ተከትሎ የመጣው የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘመቻና ጫና አምራች ድርጅቶች ተረጋግተው እንዳይሠሩና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ተፅዕኖ አሳድረዋል። በተጨማሪም ኤምባሲዎች ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ከፍተኛ ግፊት ሲያደርጉ ስለነበር አምራቾች በጫና ውስጥ ሆነው ለመሥራት የተገደዱበት ዓመት እንደነበር አይዘነጋም።

የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲቀዛቀዝ ምክንያት ለነበረው የሰላም መደፍረስ መፍትሔ ይሆናል የተባለውና ባለፈው ጥቅምት ወር በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል። የሰላም ስምምነቱ በተለያዩ ጫናዎች ሳቢያ የተቋረጡ የማምረት ሥራዎች እንዲጀመሩ፣ የተቀዛቅዙ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ሥራዎች እንዲያንሰራሩ እና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ ሀገሪቱ እንዲመጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል። እንደተጠበቀውም የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ ወዲህ ተቀዛቅዞ የነበረው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መነቃቃት ታይቶበታል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ተመስገን ጥላሁን፣ የሰሜን ኢትዮጵያው ግጭት በሰላም ስምምነት መቋጨቱን ተከትሎ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ከፍተኛ መነቃቃትና መሻሻል እየታየ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። «ጦርነቱ በኢንቨስትመንት ላይ አስከትሎት የነበረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። በወቅቱ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የነበራቸው ፍላጎት ቀንሶ ነበር። ከሕግ ማሻሻያዎች ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ የነበሩ እድሎች ሰፊ ቢሆኑም በተለይ ትልልቅ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በኢንቨስትመንት ላይ ለመሠማራት ይዘውት የነበረውን ፕሮግራማቸውን በተወሰነ መልኩ አዘግይተውታል። እንደ ሳፋሪኮም ያሉ ድርጅቶች ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በኢንቨስትመንት ላይ እንደተሰማሩ አይዘነጋም» ይላሉ።

በአሁኑ ወቅት፣ የሰላም ስምምነት መፈረሙን ተከትሎ፣ ኢትዮጵያ ወደ መረጋጋት ተሸጋግራለች ምክትል ኮሚሽነሩ፣ «ከጦርነቱ መቆምና ከሰላም ስምምነቱ መፈረም ጋር ተያይዞ ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎችን እያየን ነው። ከእኛ ጋር ግንኙነት የነበራቸው አካላት በድጋሚ ከእኛ ጋር ንግግር ጀምረዋል፤ ወደ ኢንቨስትመንት ሥራዎቻቸው ለመመለስና ወደ ተግባር ለመግባት ፍላጎት አሳይተዋል። እኛም በበቂ ሁኔታ በማገዝ ወደ ሥራ እንዲገቡ እያደረግን ነው። በተጨማሪም የአዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ፍሰት እየጨመረ ይገኛል። ከስምምነቱ መፈረም በኋላ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በየጊዜው እያደገ መጥቷል። በአጠቃላይ የሰላም መስፈን ለኢንቨስትመንት ወሳኝ እንደሆነ በተግባር እያየን ነው» በማለት የሰላም ስምምነቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን እያነቃቃው እንደሚገኝ ይናገራሉ።

የፐብሊክ ፖሊሲ ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ የሰላም ስምምነቱ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መነቃቃት በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ጠቁመው፣ የዘርፉን እድገት ዘላቂ ለማድረግ ግን ከሰላም ስምምነቱ የተሻገሩ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። እርሳቸው እንደሚገልፁት፣ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማሳደግ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካና የሰብዓዊ ዲፕሎማሲ ጥረቶች ያስፈልጋሉ። እነዚህ የዲፕሎማሲ ሥራዎች የሀገሪቱን ገጽታ ለሌላው ዓለም በበጎ መልኩ በማሳየት ሰብዓዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘት የሚያግዙ ተግባራት ናቸው።

ትልልቅ የውጭ ሀገራት ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚያያዘው የንግድና ቢዝነስ ሥራ አመቺነት (Ease of Doing Business) ነው። ተቋማዊ ቢሮክራሲን ቀላልና ፈጣን በማድረግ የንግድና ቢዝነስ ሥራን ምቹ ማድረግና የኢንቨስትመንት ፍሰትን ማሳደግ ይገባል። ለዚህም በታችኛው የአስተዳደር እርከኖች ላይ ከሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ብዙ ሥራ ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ «በሀገሪቱ በስፋት ለተንሰራፋው አደገኛ የሙስና ተግባር ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል። ትልቅ አቅም ኖሯቸው በኢትዮጵያ ውስን የሚባል የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ካላቸው ሀገራት ጋር ግንኙነትን የበለጠ ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ነው። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ከዲፕሎማቶች ብዙ ሥራ ይጠበቃል» በማለት ይመክራሉ።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የተቀዛቀዘው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲነቃቃ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ አሠራር መተግበር እንደሚያስፈልግ ይታመናል። ለዚህም የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን መቅረፅና መተግበር ያስፈልጋል። ቀደም ሲል የነበረው ሀገራዊ የኢንቨስትመንት አዋጅ መሻሻሉ የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። የኢንቨስትመንት ሕግጋት መሻሻል በድህረ ጦርነቱ ወቅት የሚኖረውን ሀገራዊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው አቶ ተመስገን ይገልፃሉ።

አቶ ተመስገን እንደሚናገሩት፣ አዲሱ የኢንቨስትመንት አዋጅ (1180/2012) ኢትዮጵያን ተወዳዳሪና ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ሊያደርጋት የሚችል ሕግ ነው። አዋጁ ለግሉ ዘርፍ በተለይም ለውጭ ባለሀብቶች ሰፊ የኢንቨስትመንት እድል የሚፈጥርና ገደብ የማያስቀምጥ አዋጅ በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ሰፊ እድል ያገኛሉ።

«ባለፉት ዓመታት ከተከናወኑ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች መካከል አንዱ በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ የተደረገው ለውጥ ነው። ቀደም ሲል ሀገሪቱ ትጠቀምበት የነበረው ፖሊሲ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው ሊሠማሩባቸው የሚችሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን የሚገድብ (Positive Listing Approach) ነበር። ይህ አሠራር ኢንቨስተሮቹ ሊሠማሩባቸው ከሚችሉባቸው ዘርፎች ውጭ ባሉት ሌሎች ዘርፎች ላይ እንዳይሳተፉ ገደብ የሚጥል ነበር።

ይህ የቀደመው አሠራር በኢንቨስትመንት አዋጁ (1180/2012) ተቀይሯል። አዲሱ የኢንቨስትመንት አሠራር ባለሀብቶች ሊሰማሩባቸው የማይችሉባቸውን ዘርፎች የመዘርዘርና የቀሩትን ክፍት የማድረግ አቅጣጫ (Negative Listing Approach) ያለው በመሆኑ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። አሁን ባለው የኢንቨስትመንት አዋጅ መሠረት ሦስት የኢንቨስትመንት ዘርፎች አሉ። እነዚህም የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በጋራ ሊሰማራባቸው የሚችሉ፣ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ የተከለሉ እና ለውጭ ባለሀብቶች ሁሉ ክፍት የሆኑ ዘርፎች ናቸው» ይላሉ።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሲዳከም ለሀገራዊ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ወሳኝ አቅም የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና አቅማቸውን ማሳደግ በጊዜ ሂደት በራስ አቅም የተገነባ ሀገራዊ የኢንቨስትመንት ዘርፍን ለመፍጠር አስተማማኝ ግብዓት ይሆናል።

በሌላ በኩል በድህረ ጦርነት ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል አንዱ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ እንደሆነ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት ሀገራት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ ትልቅ ተሞክሮ አላቸው። እንዲያውም ለአሁኑ የምጣኔ ሀብት ኃያልነታቸው መሠረት የሆናቸው ከውጭ ጥገኛነት ያላቀቃቸው የአምራችነት አቅማቸው ማደግ እንደሆነ ይታወቃል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ለማጠናከር መንግሥት በዋናነት የፋይናንስ ድጋፎችን ማድረግ እንዳለበት ይናገራሉ። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አቅም ለማሳደግ የሚያስችል የተደራጀ የመንግሥት መዋቅር መገንባት፣ በአጠቃላይ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የኢኮኖሚው ምሰሶ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ።

ከእነዚህም መካከል አንዱ የሆነው የፋይናንሱ ዘርፍ ትልቅ ሪፎርም ያስፈልገዋል ሲሉም ይገልጻሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ከሰላምና መረጋጋት ባሻገር የፋይናንስ ሁኔታው ምቹ ሊሆን ይገባል። ሕግጋትን ማሻሻል እንዲሁም ወቅቱን የሚመጥኑ ውጤታማ ባለሙያዎች ዘርፉን እንዲመሩት ማድረግ ያስፈልጋል። የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገበያ መግባታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ችግር እየገጠማቸው ይገኛል። የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ለኢንቨስትመንት ሥራዎች የተሻለ የፋይናንስ ምንጭ ይገኛል። ይህም ከኢንቨስትመንት ሥራዎቹ የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝና የሀገሪቱ የንግድ ሚዛን እንዲስተካከል ያግዛል። ‹የውጭ ባንኮች ቢገቡ የሀገር ውስጥ ባንኮችን ይጎዳሉ› የሚለው ሃሳብ ትክክል እንዳልሆነ ያስረዳሉ።

የሰላም መስፈን ለኢንቨስትመንት ማደግ የመጀመሪያውና ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው። ያለሰላም የሚታሰብም ሆነ የሚከናወን የኢንቨስትመንት ተግባር የለም። ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሠራራት ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የሰላም ስምምነት የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ ለስምምነቱ ገቢራዊነት ቁርጠኛ ከመሆን በተጨማሪ፣ ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና በብቃት መተግበር ይገባል።

# ለትንሿ ዳቦ ከምንጋደል ኑ!

## ትልቅ ዳቦ እንጋግር

ምሕረት ሞገስ

ገና ሳይመሽ ጭጋግ ያጨለመው ግሮሰሪ፤ እነተሰማ መንግሥቴን፤ ዘውዱ መታፈሪያንና ገብረየስ ገብረማሪያምን ጨምሮ የዘወትር ደንበኞች በጊዜ ታጭቀው ስላጨናነቁት በሰዎች ትንፋሽ ታፍኗል። ሁሉም እየጮሁ ያወራሉ። ብዙዎቹ ደምስራቸው በግንባራቸው ላይ ተገታትሯል። የበዓል ድባብ አልጠፋም። ብልጣብልጡ የግሮሰሪው ባለቤት ለጠጪው ዳቦ በትንንሹ ሸንሽኖ በአስተናጋጆቹ በኩል እያከፋፈለ ነው።

ተሰማ የብልጣብልጡን የግሮሰሪ አትራፊ የፈጠረውን አጋጣሚ ተከትሎ ትልቅ ዳቦ ስለመጋገር አሰበ። ‹‹ወገን ከወገን ጋር ተባብሮ ትልቅ ዳቦ መጋገር አለበት። የሚያዋጣው በትንሿ ዳቦ ምክንያት መገዳደል ሳይሆን፤ ትልቅ ዳቦ መጋገር ነው። ትልቅ ዳቦ ለመጋገር ደግሞ ትልቅ ንቅናቄ ያስፈልጋል።›› አለ።

ዘውዱ ከት ብሎ ሳቀ። ‹‹ትልቅ ዳቦ ለመጋገር ብዙ ዱቄት እና በደንብ የታሰሰ ምጣድ ያስፈልጋል፤ የታሰሰ ምጣድ እና ብዙ ዱቄት ከየት እናምጣ?›› በማለት ጥያቄ አቀረበ። ተሰማ፣ ‹‹የሥራ ንቅናቄ መፈጠር አለበት። ዜጎች 24 ሰዓት የሚሠሩበት ሁኔታ ከተመቻቸ ብዙ ዱቄት ማግኘትም ሆነ ትልቅ ዳቦ መጋገር የሚያስችል ትልቅ ምጣድ ማሟሸት አያዳግትም።›› በማለት ምላሽ ሰጠ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹በቅድሚያ መጋደልን ምን አመጣው? የሚለውን ጥያቄ ቀድሞ መመለስ ያስፈልጋል። ሰው ከሥራ ለራሱ አያንስም። ለራሱ ትንሽ ዳቦ መጋገር አያቅተውም። 24 ሰዓት ቀርቶ ለስምንት ሰዓት በትክክል ከሠራ ከራሱ አልፎ ለሰው ይተርፋል። በሽታ የሆነብን ሁላችንም ያልሠራነውን ያህል መፈለጋችን ነው። ችግሩ ሥራ አለመውደድ ነው። ወጣቱ የወደፊት ዕድሉን ለማቃናት ከመሥራት ይልቅ፤ በማይገባው እየገባ ፖለቲካውን ሲያራግብ የመሥሪያ ሰዓቱ ያመልጠዋል። ሌላውም የራሱን ኃላፊነት መወጣት ሲኖርበት በተቃራኒው በወሬ ጊዜውን ሲገፋ የሚበላው ያጣል። በጥቂቶች የተጋገረው ትንሽ ዳቦ ለብዙኃኑ አይበቃም፤ መቧጨቅ ይሆናል። አገር የምታድግበት ዕድል ይጠባል። ድህነት በላይ በላዩ ይደራረባል። ሃብት ሲያንስ ወንድማማችነት ቀርቶ ወደ ጦርነት መግባት ግድ ይሆናል›› አለ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ፀረ ጦረኛ ወይም ከጦርነት ውጪ ለመሆን አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት እና ትልቁን ዳቦ በመጋገር ሕዝብ ለማጥገብ ያለፈው አልፏል በሚል መንፈስ፤ ይቅር ተባብሎ ወደ ፊት መቀጠል የግድ ነው። ያለበለዚያ በማሸነፍ ሁሉን መቆጣጠር ቢቻል እንኳ ከፊል ሰላም እንጂ ሙሉ ሰላም ማምጣት ያዳግታል።›› አለ። ዘውዱ ግን፤ ‹‹ሰላም አስፈላጊ መሆኑንማ ማንም አያጣውም። ለአንድ አገር ሕዝብ ሰላም አስፈላጊው መሆኑን መናገር ተራ ጉዳይ ነው፤ ሁሉም ያውቀዋል። ሰላም ከሌለ ለሕዝብ ብቻ አይደለም፤ መንግሥት ፖለቲካውን ከላይ ሆኖ ለመምራት ቢሞክርም አይሳካለትም። ምክንያቱም ሰላም ሳይመጣ በጉልበት ላይ ተማምኖ ኃይል መጠቀም ስምምነት ስለማያመጣ፤ አመፅ የሚያጋጥምበትን ጊዜ ለመተንበይ ያስቸግራል። ይህ ደግሞ ለመንግሥትም ትልቅ ስጋት ነው። ዋናው ጉዳይ ግን የተጎዳው ተጎዳ ያለፈው አለፈ ብሎ ለመዝጋት የተጎዱትን መካስ የግድ ነው። ቢያንስ በኑሯቸው መደገፍ ያስፈልጋል›› አለ።

> ፀረ ጦረኛ ወይም ከጦርነት ውጪ ለመሆን አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት እና ትልቁን ዳቦ በመጋገር ሕዝብ ለማጥገብ ያለፈው አልፏል በሚል መንፈስ፤ ይቅር ተባብሎ ወደ ፊት መቀጠል የግድ ነው። ያለበለዚያ በማሸነፍ ሁሉን መቆጣጠር ቢቻል እንኳ ከፊል ሰላም እንጂ ሙሉ ሰላም ማምጣት ያዳግታል

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹እርሱማ ምን ጥያቄ አለው። ሰላም ስለመጣ ሌሎች ሞተዋል እና አሁንም ሞት ይቀጥል ማለት አይገባም። ለቆመው ‹ሞት አነሰው› ካልን አያዋጣም፤ ሰላም መፍጠር ተንኮለኝነት ወይም ክፉነት አይደለም። አታላይ እና ውለታ ቢስነት ሊሆንም አይችልም፤ የሰውን ደም ደመከልብ ማድረግም አይደለም፤ ደግ ማሰብ እና ለጥሩ ነገር መታገል መልካም ነው። ቂም ይዞ መለያየት እና መጣላት አትራፊ ሆኖ አያውቅም። ለሰው ልብሱ ሰው ነው። ለሰው ጉልበቱ፣ ድምቀቱና ሕልውናው ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት እና በሌሎች ሰዎች ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ነው። በመደጋገፍ ትልቅ ዳቦ መጋገር ቢሳነን እንኳ ከምንገዳደል ለየራሳችን የሚበቃ ቢያንስ ትንሽ ዳቦ እንጋግር፤ ...›› ብሎ ሊቀጥል ሲል ተሰማ በደስታ በገብረየስ ሃሳብ በመስማማት እርሱም ለማለት የፈለገውን ማተት ቀጠለ።

‹‹ከምንባላ እንስማማ በትንሿ ዳቦ ላይ ከምንጋደል በስምምነት ትልቅ ዳቦ እንጋግር ያልኩት ለዚሁ ነው።›› አለ ተሰማ ዘውዱን እያየ። ዘውዱ ደግሞ ‹‹ለስሚ መጠሪያ ቁና ሰፋች አይነት ነገር እንዳይሆን መጠንቀቅ የግድ ነው። ለመታየት እና ለመታወቅ ሲባል የሚፈፀም ድርጊት ፍፃሜው አያምርም። መታረቅ ከልብ መሆን አለበት። ትልቅ ዳቦ ለመጋገር መስማማትና የሚጋገርበት ምጣድ እንዳይሰበር መጠንቀቅ ይገባል። ምጣድ ከተሰበረ እርቅም ጠብም ቅንጦት ነው። ወጣት ወይም የተማርኩ ንቁ ስለሆንኩ ሁሉን በግድ አስፈፅማለሁ ማለት ብዙ ርቀት አያስጉዝም። ማደግ፣ መወፈር እና መዳበር ቢቻልም፤ ዱላ ካለ ለመከላከል በሚደረግ ያላሰለሰ ጥረት መድከም አይቀርም።

ለእዚህ መፍትሔው ሰላም እና የዜጎችን ነፃነት ማረጋገጥ ነው። ምጣዱ ሳትሰበር እንድትቆይ እና ትልቅ ዳቦ ለመጋገር በነፃነት መነጋገር እና ይቅር መባባል ያስፈልጋል።›› ብሎ ዘውዱ ሊቀጥል ሲል፤ ተሰማ ሳይቀደም ፈጠን ብሎ ‹‹ትልቅ ዳቦ ለመጋገር የሰላም ስምምነት በመፍጠር ሂደት ውስጥ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ እና ወዘተን የመሳሰሉ ነፃነቶችን ማክበር የግድ ነው። ሰላም ለማምጣት መመሳጠር ጦርነት ለማወጅ በእልህ ከመወጣጠር ጋር በእጅጉ ይቃረናል። ለሰላም ሲባል መተሳሰር ምጣዷ እንዳትሰበር መጠንቀቅ በምንም መልኩ አያስነቅፍም። ነገር ግን ትልቁን ዳቦ ለመጋገር የተወጠነ መደራጀት፣ የተወጠነ እና በደንብ የታሰበበት አመራርነት እና የመመራት ጥበብ ያስፈልጋል።›› አለ።

ተሰማ ቀጠለ፤ ‹‹ የተወጠነ ሰላም መፍጠር በደንብ ከታሰበበት ከተወጠነ አመራርነት ጋር የሚያያዝ ነው። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው በጣም አስገራሚ የመመራትም ሆነ የመምራት ጊዜያትን አሳልፈዋል። ነገር ግን አሁን በሚታየው ደረጃ ላይ ደርሰናል። ኢትዮጵያውያን ለትውልድ የሚተርፍ ዕዳን አከማችተናል፤ በድህነት ስመ-ጥር በኢኮኖሚያዊ ሃብት ደግሞ ጭራ ሆነናል። የዚህ ሁሉ ምክንያት ዘመናችንን በጦርነት ማሳለፋችን ነው። ደርሰን የሚቀናን ጦርነት ነው። ዳቦ ለመጋገር ከመሯሯጥ ይልቅ የሚያለያይ ነገር ፈልጎ መራቆትን ልማድ አድርገነዋል። ሰበብ እየፈለጉ፤ ብሔር እና ሃይማኖት እየጎተቱ አፍንጫ መንፋት፣ በመተባበር የወደፊቱን አስቦ ከመሥራት ይልቅ የመለያያ ቀዳዳ እየፈለጉ ነገር እያወሳሰቡ ልዩነትን ማስፋት በተለይ የተማረው ኅብረተሰብ የብቃት መለኪያ ሆኗል።

ነገር ግን አዋቂነት ነባራዊውን ሁኔታ መረዳት ነው። የሀገርን ነባራዊ ሁኔታ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ አስመልክቶ ማሰብ ብቻ ሳይሆን የግድ ማሰላሰል ያስፈልጋል። ቢያንስ የውጪ ጠላትን አሳፍሮ አገርን በሰላም ለማቆየት የውስጥ ስምምነት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ይህ በፍፁም የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም።›› በማለት ለማሳመን ጥረት አደረገ።

ዘውዱ በበኩሉ፤ ‹‹የውጪ ጠላቶች ጉዳይ እንዲህ በእኔና በአንተ ለዛውም በእዚህች ትንሽ ዕይታ እና ጊዜ የሚብራራ አይደለም። እርግጥ ነው፤ ፍላጎታቸው ኢትዮጵያውያንን ማባላት ነው። እኛ ደግሞ ለመባላት ዝግጁ ነን። ያለፉ መንግሥታት ምንም ቢያጠፉ ኢትዮጵያ እንዳታድግ የሆነበት ትልቅ ምክንያት ሰላም ማጣታችን ነው። መንግሥታት ኃይላቸውን የሚጨርሱት በልማትና ኢትዮጵያን በማሳደግ ላይ ሳይሆን ምጣዷ እንዳትሰበር በመጠንቀቅ ለርሷ የኃይል ከለላ በማድረግ ሲታገሉ በውጪ ጠላቶች ግፊት ያልፋሉ። ኢትዮጵያውያን የዳበረው መጥቶ በአዲስ ለተተካው መንግሥትም ከጎን በመቆም አገር እንድታድግ ከመሥራት ይልቅ በተቃራኒው በተቃውሞ ይቆማሉ። መንግሥትም ከመዳበር ይልቅ ይሸመደመዳል። በሂደት ምጣዷ እንድትሰበር ዕድል ይፈጠራል።›› ሲል ተሰማ ዘውዱ በሰጠው ሃሳብ በመደሰት ፊቱ በፈገግታ ተሞላ።

‹‹አሁን እየገባህ ነው።›› አለ ተሰማ፤ ዘውዱ ግን ‹‹እኔ ሰላም አያስልፈልግም አላልኩም። ሰላም እና ዕርቅ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም። የእኔ ጥያቄ ሌላ ነው። ለሕዝቡ ለምን አይታሰብም የሚል ነው።›› አለ። ተሰማ ጥያቄ አቀረበ። ‹‹ለሕዝብ ማሰብ ማለት ምን ማለት ነው? ከዚህ በላይ ማሰብ እንዴት ይቻላል? ሰላምን እንመርኮዝ እያልን ነው። ይህ ያለምንም ጥያቄ ለሕዝብ ማሰብ ነው። ሰላም ከሆነ ለልማት ሰፊ ጎዳና ለማግኘት አያዳግትም። ግልጹ ጉዳይ ሰላም ከሌለ ልማት የለም። ዘመናት የሚያልፉት በጥፋት ብቻ ይሆናል። ይህ አሁን ላለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድም መከራ እና ፍዳን ማስቀመጥ ነው።›› በማለት በንዴት እና በኃይል ለመናገር ሞከረ።

ዘውዱ ግን ለስለስ ብሎ ‹‹ትልቅ ዳቦ ለመጋገር ዋነኛው ጉዳይ የኑሮ ዋስትና ነው። የኑሮ ዋስትና ከተረጋገጠ ከመሐል ከተማ እስከ ዳር ጠረፍ በነፃነት መንቀሳቀስ፣ በነፃነት መሥራት ከተቻለ ዕዳው ገብስ ነው። ይህ ሳይሆን የዜጎችን የተሟላ ኑሮ ማረጋገጥ ይቻላል ብሎ ማሰብ ቀልድ ነው። የተሟላ ኑሮን ለመምራት ሳይሞከር ትልቅ ዳቦ ስለመጋገር ማውራትም ከተረተረት ያለፈ አይሆንም።›› ሲል በዘውዱ ንግግር ተሰማ ይበልጥ ቆጣ አለ።

‹‹ትልቅ ዳቦ ስለመጋገር ስገልፅ መነሻዬ ሕዝብን መጨቆን ላይ ተመርኩዤ አይደለም። ሰላም፣ ፍትሕ፣ ነፃነትና እኩልነት መኖር እንዳለበት የእኔም እምነት ነው። ያለበለዚያ የሚሠራው ሁሉ ውሎ አድሮ በአሸዋ ላይ እንደተገነባ ቤት ሊናድ እንደሚችል አምናለሁ። ስለዚህ አሁን ውስጣዊ አንድነት ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ነው። ይህንን ጥረት እንደግፈው፤ እንደጋገፍና ፊታችንን አገርን ወደ ማሳደግ እናዙር፤ ያለበለዚያ ጨቅላ ተስፋዎችን እየቀጨን ካኮላሸን መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ሕልውናም አደጋ ላይ ይወድቃል። እያልን ነው።›› በማለት ተሰማ የሚያምንበትን ለማሳመን በቁጣ አዘል ድምፀት ሃሳቡን ገለፀ።

ዘውዱ በበኩሉ፤ ‹‹ጨቅላ የሰላም ተስፋዎችን የመቅጨት ፍላጎትም ሆነ አላማ የለኝም፡፡ ነገር ግን የመናገር ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ ኑ! ትልቅ ዳቦ እንጋግር ብለሃል፡፡ በዚህ ሃሳብ እስማማለሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ ፍትህን ወይም ነፃነትን በሚመለከት ጥያቄ ማቅረቤን እንደሃጢያት ከቆጠርከው ያው ጠላት ሆንን ማለት ነው፡፡ የኔን ሃሳብ ባትቀበል እንኳን ለማዳመጥ ዝግጁ ሁን፡፡ ያለበለዚያ ወጣትነትና ባለሙሉ ሃይልነት ዘላቂ አይደለም፡፡ መድከም ማርጀት ይመጣል፤ የዛን ጊዜ የኔ ልጅ ፈርጥሞ የኔን ሃሳብ በመቃወምህ ዋጋ ያስከፍልሃል፡፡ ስለዚህ ለዚህ መሠረቱ ሰላም፤ ከሰላም ጋር ነፃነት እና ፍትህን ማረጋገጥ ነው፡፡›› ብሎ እንደልማዱ የብርጭቆውን ድራፍት ጨልጦ ቀድሞ ተነሳ፡፡ ‹‹ሳይመሽ ብገባ ይሻለኛል፤›› ብሎ ከግሮሰሪው ወጣ፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ተተኪ ድምፃውያንን በ«ባላገሩ ምርጥ»

አስናቀ ፀጋዬ



**ተተኪ ድምፃውያን እየጠፉ በመጣበት በዚህ ጊዜ ባላገሩ ምርጥን የመሰሉና ሌሎች መሰል የሙዚቃ ባለተሰጥኦ ወድድሮች ተተኪ ድምፃውያንን በማፍራት ረገድ ሚናቸው የጎላ ነውና ተጠናክረው ሲቀጥሉ እንጂ ሲኮስሱ አይገባም**

የሰዎችን ቀልብ ከሚገዙና አዝናኝ የኪነ ጥበብ ዘውጎች ውስጥ አንዱ ሙዚቃ ነው። ሙዚቃ ከአዝናኝነቱ ባሻገር በርካታ ማህራበዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎችም ሀገርኛ መልዕክቶች የሚተላለፉበት የጥበብ ዘርፍ ነው። በሙዚቃ ፍቅር፣ አንድነት ፣ መተሳሰብና አብሮነት ይሰበካል። በሙዚቃ የግል ስሜት፣ ደስታ፣ ፍቅር፣ አስተሳሰብ፣ ሃሳብ ያለገደብ ይገለፃል። በሙዚቃ የራስን ሁለንተናዊ ስሜት ከማንፀባረቅ ባለፈ የሌሎችንም ስሜት መኮርኮር፣ ማነሳሳት፣ ማነቃቃትና ማበረታታት ይቻላል። ለዛም ነው ሙዚቃ የአለም ቋንቋ ነው የሚባለው።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሙዚቃ ታሪክ ቀደምት ሙዚቀኞች በጊዜያቸው እንደየራሳቸው ቀለምና የአዘፋፈን ስልት በማቀንቀን የራሳቸውን የጥበብ አሻራ አስቀምጠዋል። የእነርሱን ፈለግ ተከትለውም በርካታ ተተኪ ሙዚቀኞች ተፈጥረዋል። እነርሱም በተራቸው አቀንቅነው የሚዚቃን ጥበብ ጥግ በራሳቸው መንገድ አሳይተዋል። አሁንም የዚህ ትውልድ ሙዚቀኞች በቀደምት የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ሙዚቃ ራሳቸውን ገርተው አያሌ የሙዚቃ ስራዎችን እንካችሁ ብለዋል።

ምንም እንኳን የዚህ ዘመን አብዛኛዎቹ ሙዚቀኞች በራሳቸው ነጠላ ዜማና ቀደምት የኢትዮጵያ ሙዚቃዎችን በራሳቸው መንገድ ዳግም ዘፍነው የአድማጫቸውን ቀልብ ለመሳብ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ከጥቂቶቹ በስተቀር እንደበፊቱ በራስ ሙሉ አልበም ሰርቶ አዳዲስ የሙዚቃ ስራዎችን ይዞ ብቅ ማለት ብርቅ እየሆነ የመጣ ይመስላል። ተተኪ ድምፃውያንን ለማፍራት የሚደረገው ጥረትም ያን ያህል አይደለም።

በእርግጥ ከአመታት በፊት ተጀምሮ ተቋረጠ እንጂ በኢትዮጵያ ቴሌቪዢን ሲተላለፍ የነበረው የኢትዮጵያ አይዶል የሙዚቃ ውድድር አዳዲስና ተተኪ ሙዚቀኞችን በማፍራት ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። የኮካ ኮላ የሙዚቃ ባለተሰጥኦ ውድድርም በተመሳሳይ ተጀምሮ ተቋረጠ እንጂ እርሱም ቢሆን ሙዚቀኞችን በማፍራት በኩል የድርሻውን ተወጥቷል።

ቀደም ሲል ሲደረጉ የነበሩ የሙዚቃ ባለተሰጥኦ ውድድሮች ከተቋረጡ በኋላ ግን ከቅርብ አመታት ወዲህ እንደገና ወደ ቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለዋል። ለዚህም በፋና ቴሌቪዥን «የፋና ላምሮት» የሙዚቀኞች ውድድር፤ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ኋላ ላይ ደግሞ በባላገሩ ቴሌቪዥን «የባላገሩ ምርጥ» ወድድር ተጠቃሽ ናቸው።

በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያን አይድል የሙዚቀኞች ውድድር ከተቋረጠ ወዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲህ አይነቱን ውድድር «ባላገሩ ምርጥ» በሚል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መጀመርና በሂደት ደግሞ በባላገሩ ቴሌቪዥን መቀጠል የተመልካቾችን ቀልብ በመሳብ ረገድ ትልቅ ድርሻ ወስዷል። በዚህ የሙዚቃ ባለተስጥኦዎች ውድድርም እንደነ ዳዊት ፅጌንና ኢሳያስን የመሰሉ በርካታ ወጣት ድምፃውያንን ማፍራት ተችሏል።

ባላገሩ ምርጥ የሙዚቃ ባለተሰጥኦዎች ውድድር ከተጀመረ ወዲህ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ የራሳቸውን አሻራ እያስቀመጡ ያሉ በርካታ አዳዲስ ድምፃውያንን እያፈለቀ ይገኛል። ሆኖም በኮቪድና በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የዘንድሮው ውድድር ደብዝዟል። እንደከዚህ ቀደሙም በየክፍለሀገሩ ተዟዙሮ ባለተሰጥኦዎችን የመፈለግ እድልም አልነበረም። ውድድሩ ረጅም ጊዜ የፈጀውም በዚሁ ምክንያት ነው። በተቻለ አቅም ግን ባለተሰጥኦዎች ከየቦታው ተሰብስበው እንዲመጡና በውድድሩ እንዲሳተፉ በባላገሩ ቴሌቪዥን በኩል ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።

የዘንድሮው የባላገሩ ምርጥ የባለተሰጥኦ ሙዚቀኞች የመጨረሻው መጀመሪያ ውድድር በባለፈው የትንሳኤ በአል በቦናንዛ ሆቴል በቀጥታ ስርጭት ተካሂዷል። በውድድሩም ካምፕ ገብተው ስልጠና ሲወስዱ ከቆዩት ሃያ ሰባት ተወዳዳሪዎች መካከል አስራ አምስቱ ተለይተው ስራቸውን አቅርበዋል። ከአስራ አምስቱ ውስጥ ለግማሽ ፍፃሜ ውድድር አላፊ የሆኑት አስር ምርጦች ታውቀዋል። አራት ተወዳዳሪዎች ደግሞ ከእድሜ በታች ሆነው በአስተሳሰባቸውና በሙዚቃ በሚያስተላልፉት መልዕክት በልዩ መልኩ ተመርጠው ለመጨረሻው ውድድር እንደሚቀርቡ ተረጋግጧል።

በሁለት ወር ጊዜያት ውስጥ ደግሞ ከአስሩ ባላገሩ ምርጥ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አሸናፊዎቹ እንደሚለዩ ይጠበቃል። በውድድሩ የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች ምንም ልምድ የሌላቸውና ከዚህ በፊት ከሙዚቃ መሳሪያ ጋር ተገናኝተው የማያውቁ በመሆናቸው ብሎም በካምፕ ገብተው ስልጠና የሚወስዱ እንደመሆናቸው ውድድሩ ትንሽ ጊዜ ይፈጃል። ነገር ግን ደግሞ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከምርጥ አስሮቹ ውስጥ በደምብ የተዘጋጁና ታሽተው የመጡ ተወዳዳሪዎች አሉ። በቀጣይ ከምርጥ አስሮቹ ውስጥ አሸናፊዎቹን ለመለየት ለዳኞች ፈታኝ የሚሆንበት ሁኔታም ተፈጥሯል። የተወዳዳሪዎች ችሎታም ተመሳሳይና ተቀራራቢ መሆኑ ተነግሯል።

የባላገሩ አስሩ ምርጥ ውድድር በቅርቡ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ የመጨረሻዎቹ ስድስቱ አሸናፊዎች በዳኞች ይለያሉ። ለመጨረሻው ውድድር የሚቀርቡትም ስድስቱ ተወዳዳሪዎች ናቸው። እነዚህን ውድድሮች ለማካሄድ ሁለት ወር ያስፈለገበትም ምክንያት በመሃል የተወዳዳሪዎቹን ማንነት ለተመልካች ማሳወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ከዚህ ባለፈ ተወዳዳሪዎች ተመልካች አውቋቸው በአጭር የፅሁፍ መልዕክት እንዲመርጣቸው የሚቀሰቅሱበት የአየር ሰአት ጊዜ ለማመቻቸትም ጭምር ነው።

ለተወዳዳሪዎች የህዝብ ድምፅ የሚፈለግ ቢሆንም በባላገሩ ምርጥ ህዝብ ተወዳዳሪዎችን የሚመርጥበት መቶኛ ነጥብ አለ። ነገር ግን ተወዳዳሪዎች ይበልጥ የሚዳኙት በሙያተኞች ነው። ተወዳዳሪው የሚገኝበትን አካባቢ ወይም ብሄሩን ተከትሎ መምረጥ አይፈቀድም። ስለሆነም ህዝቡ ተወዳዳሪዎችን እንዲመርጥ 7544 አጭር የፅሁፍ መልእክት ተዘጋጅቷል።

በባላገሩ ምርጥ የሙዚቀኞች ባለተሰጥኦ ውድድር አሸናፊ ለሚሆኑ ተወዳዳሪዎች በጥቅሉ ስምንት ሚሊዮን ብር ተመድቧል። በወድድሩ አንደኛ የሚወጣውን ተወዳዳሪ ጊፍት ሪል እስቴት የሚሸልም ሲሆን ሁለተኛና ሶስተኛ የሚወጡትን ተወዳዳሪዎች ደግሞ ሌሎች ወድድሩን ስፖንሰር ማድረግ የሚፈልጉ ድርጅቶች እንዲሸልሙ ተጋብዘዋል።

ሽልማቱ ተወዳዳሪዎች ብዙ በደከሙበት ልክ እና እስከመጨረሻው ድረስ እንዲሄዱ ታላሚ ባደረገ መልኩ ተዘጋጅቷል። ተወዳዳሪዎች የተሻለ ቦታ ላይ ደርሰው ሀገራቸውንም ጭምር ሊያስጠሩ የሚያስችልም ጭምር ነው። በዚሁ መሰረት ከአንደኛ እስከ አራተኛ ደረጃ ይዘው የሚያጠናቅቁ ተወዳዳሪዎች ይሸለማሉ። ከአራተኛ እስከ አስረኛ ደረጃ ይዘው የሚያጠናቅቁ ተወዳዳሪዎችም በባዶ አይሸኙም።

በውድድሩ አንደኛ ሆኖ ለሚያጠናቅቅ ተወዳዳሪ የሶስት ሚሊዮን ብር ሽልማት ተዘጋጅቷል። ከዚህ ውስጥ ተወዳዳሪው አንድ ሚሊዮን ብሩን ለራሱ የሚወስድ ሲሆን ቀሪው ሁለት ሚሊዮን ብሩ በቀጣይ አልበም መስሪያ፣ ለዜማ፣ ግጥም ለስቱዲዮ ክፍያ ይውላል። ሁለተኛ ሆኖ የሚያጠናቅቀው ተወዳዳሪ ደግሞ ሁለት ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ይሆናል። ከዚህ ውስጥ አምስት መቶ ሺ ብሩ ለራሱ ይደርሰዋል። ቀሪው አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብሩ ደግሞ በተመሳሳይ ለአልበም ስራ ይውላል። ሶስተኛው የውድድሩ አሸናፊ አንድ ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሲሆን ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ ብሩ ለራሱ፤ ቀሪው ሰባት መቶ ሀምሳ ሺ ብሩ ደግሞ ለሙሉ አልበም ማሰሪያ ይሆናል።

የሶስቱም አሸናፊዎች ሙሉ አልበም በያሆ ኢንተርቴይመንት አማካኝነት ይሰራል። ከሀገር ውስጥ ጀምሮ በተለያዩ አውሮፓ ሀገራትና በአሜሪካ በተቀናጀና በውጪ ሀገር በሚገኙ ባለሙያዎች እገዛ አሸናፊዎች የኮንሰረት ስራዎችን እንዲያቀርቡ ይደረጋል። ከአራት እስከ አስር የሚወጡ ተወዳዳሪዎችም ሁለት ነጠላ ዘፈኖችን እንዲሰሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

በውድድሩ አንደኛና ሁለተኛ የወጡ ተወዳዳሪዎች ሙሉ የአልበም ኮንትራት ይፈርማሉ። ሶስተኛ የወጣው ተወዳዳሪም እንደ ሽልማቱ መጠን ታይቶ ሶስት ወይም አራት ነጠላ ዜማዎችን ይሰራል። ከአንድ እስከ አስር የወጡት ግን የጋራ ሙሉ አልበም ይሰራሉ። ይህም ከአራት እስከ አስር የወጡ ተወዳዳሪዎችን ለአድማጭ ተመልካች ለማስተዋወቅ ያግዛል።

ከዚህ በፊት በባላገሩ ምርጥ ውድድር ከአንድ እስከ ሶስት የወጡ ተወዳዳሪዎች ብቻ ይሸለሙ የነበረ ቢሆንም በዚህ ውድድር ግን ከአራት እስከ አስር ለወጡ ተወዳዳሪዎችም ለእያንዳንዳቸው የመቶ ሺ ብር ሽልማት ይበረከትላቸዋል። በዚሁ ውድድር አራት ልዩ ተሸላሚዎችም ይኖራሉ። ሶስት የተለያዩ ሙሉ አልበሞችም ከአንድ እስከ ሶስት በወጡ ተወዳዳሪዎች ይሰራሉ። እንደየዘፈኖቹ ጉልበት ታይቶም የሚሰሩ የተለያዩ የሙዚቃ ክሊፖችም ይኖራሉ።

የዚህ ወድድር ሽልማት ዋነኛ አላማውም ተወዳዳሪዎች ስለድምፃቸውና ስለስራቸው እንጂ ስለሌላው ጉዳይ እንዳይጨነቁ ነው። ዜማ ደራሲውንና ገጣሚውን አሰባስቦ፣ ስቱዲዮና ሙዚቃ አሬንጅመንት ዝግጁ አድርጎ የሚያሰራ ቡድን ተዋቅሯል። ለተወዳዳሪ የሚሰጣቸው ሽልማትም በዚሁ በሚዋቀረው ሙዚቃ ቀማሪ ቡድን በትንሽ ወጪ አልበማቸውን ለማሰራት ያስችላቸዋል። ለዛም አሸናፊዎች ከሚያገኙት ሽልማት ውስጥ የተወሰነው ነው ለአልበም ማሰሪያ የሚውለው።

ከዚህ በኋላም ከአልበሙ ሽያጭ አሸናፊው ሙዚቀኛ የሚያገኘው ገቢ ይኖራል። ከአልበሙ ስራ በኋላም አልበሙ እየተወደደ ከሄደ በኮንሰርት ስራዎች ከሙዚቀኛው ጋር በመስማማት ልዩ የክፍያ ኮንትራት ይኖራል።

የሙዚቃው ዘርፍ በተደጋጋሚ የተተኪነት ጥያቄ በሚቀርብበት በዚህ ጊዜ በሀገሪቱ ጦርነት፣ ግጭትና መፈናቀል ብሎም ሰላም በጠፋበት ወቅት እንዴት ይካሄዳል የሚል ሌላ ጥያቄ ይነሳበታል። ውድድሩን ለማዳከም የሚደረጉ ጥረቶችም ይስተዋላሉ። ነገር ግን ደግሞ በቀውስም ወቅት ቢሆን ሙዚቃ ሰላም በመስበክ፣ ህዝብን በማቀራረብና አንድ በማድረግ ረገድ ሚናዋ የጎላ ነው። እነ ጥላሁን ገሰሰ፣ መሃሙድ አህመድ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ ሂሩት በቀለ፣ አለማየሁ እሸቴ፤ ከአሁኖቹ ደግሞ እነ ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ማዲንጎ አፈወርቅ፣ ታምራት ደስታና ሌሎችም ድምፃውያን ደግሞ ተተኪዎችን በማፍራቱ ሂደት የድርሻቸውን ተወጥተዋል።

እናም ተተኪ ድምፃውያን እየጠፉ በመጣበት በዚህ ጊዜ ባላገሩ ምርጥን የመሰሉና ሌሎች መሰል የሙዚቃ ባለተሰጥኦ ወድድሮች ተተኪ ድምፃውያንን በማፍራት ረገድ ሚናቸው የጎላ ነውና ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንጂ ሊኮስሱ አይገባም። የኢትዮጵያ አይድል ውድድር ሲጀመር እንኳን በርካታ የተረሱ የቀድሞ ሙዚቀኞች በተወዳዳሪዎች ታውሰዋል። የህዝቡም ጆሮ በምን ያህል ደረጃ ለሙዚቃ እንደተቃኘ ታይቷል። ስለዚህ በተሰጥኦ ውድድሮች የተተኪ ሙዚቀኞች ፍሊጋ ተጠናክሮ ይቀጥል እንላለን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ከበሽታ በላይ እየገደለ ያለ በሽታ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የመንገድ ትራፊክ አደጋ አሁንም ዋነኛ ዓለም አቀፍ የማኅበረሰብ ችግር ነው። አደጋው ለበርካታ ሰዎች ሕይወት መጥፋትና አካል መጉደል መንስኤ ሲሆን አሁንም የእለት ተእለት አሳዛኝ ክስተት እንደሆነ ቀጥሏል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ በአማካይ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሰዎች በትራፊክ አደጋ እንደሚሞቱ በቅርቡ የወጡ አኃዛዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከ30 እስከ 50 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ ለአካል ጉዳት እንደሚዳረጉ፤ የትራፊክ አደጋ ከሀገራት አጠቃላይ ምርት በአማካይ ከሦስት እስከ አምስት በመቶ ያህሉን እንደሚሳጣም እነዚሁ መረጃዎች ያሳያሉ።

የትራፊክ አደጋ በኢትዮጵያም ዋነኛ የሞት መንስኤ ከሆነ ሰነባብቷል። በዚሁ አደጋ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በትራፊክ አደጋ ምክንያት በየዓመቱ ሕይወታቸው ይቀጠፋል። ከአሽከርካሪ ሥነ-ምግባር ጋር የተያያዙና ሌሎችም ምክንያቾች እንዳሉ ሆነው ከፍጥነት ወሰን ገደብ በላይ ማሽከርከር ለአደጋው ዋነኛ መንስኤ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል።

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ዋና ዋና መንስኤዎች ላይ ያተኮሩ፣ ውጤታማነታቸው በተረጋገጡና መረጃ ላይ መሠረት ያደረጉ የመንገድ ደህንነት የመፍትሔ ርምጃዎችን በመውሰድ አደጋውን መከላከል እንደሚቻል ብዙዎች ይስማማሉ። ጉዳዩ የተለያዩ ተቋማትን ያሳተፈ ፈርጀ ብዙ ሥራዎችን ተግባራዊ መደረግንም ይጠይቃል።

ለዚህ ደግሞ መረጃ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ከግምት ውስጥ በማስገባት የጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርስቲ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳት ምርምር ተቋም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኅብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት ጋር በመተባበር የአሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪዎች ተጠቃሚዎችን የመንገድ አጠቃቀም የመንገድ ዳር ዳሰሳ ጥናት እ.ኤ.አ ከ2015 እስከ 2022 ለሰባት ዓመታት ሲያካሂድ ቆይቶ የጥናቱን ውጤት በቅርቡ ይፋ አድርጓል።

በትራፊክ ግጭት ዋና ዋና መንስኤዎች ላይ ማለትም በፍጥነት ማሽከርከር፣ የደህንነት ቀበቶና የልጆች የደህንነት



መቀመጫ እና የጭንቅላት መከላከያ ቆብ አጠቃቀም ላይ የመንገድ ዳር ምልከታ ተደርጎ በተለይ በአዲስ አበባ ለሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች ዋነኛ ምክንያት አሁንም ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር መሆኑና ችግሩ አሁንም መቀጠሉ ተጠቁሟል። ይኸው የዳሰሳ ጥናት 59 በመቶ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ከፍጥነት ወሰን በላይ ሲያሽከረክሩ መስተዋላቸውንና ይህ አኃዝ በተከታታይ እየጨመረ ስለመምጣቱ አሳይቷል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኅብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት መምህርና ዋና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ዋቅጋሪ ደሬሳ ከፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር ለሚደርሰው አደጋ አሽከርካሪዎች ትልቁን ድርሻ ቢወስዱም ከመንገድ ሁኔታና ከትራፊክ መጨናነቅም ጋር ይያያዛል። የትራፊክ መጨናነቅ ሲባል አሽከርካሪዎች በፍጥነት ወደ ሥራ ቦታቸውና ወደተለያዩ ጉዳዮቻቸው ጋር ለመድረስ ከትራፊክ መጨናነቁ ለማምለጥ በፍጥነት ሲያሽከረክሩ አደጋ ሊደርሱ ይችላሉ።

ነገር ግን ይህ የአሽከርካሪዎቹ ሁኔታ በትክክል ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ አደጋው እንዳይከሰት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ የሚገኙት። ለአብነትም በተለያዩ ቁልቁለታማ የከተማዋ መንገዶች ላይ ፍጥነት መቀነሻዎች ተሥርተዋል። እንደዛም ሆኖ ግን የአሽከርካሪዎች የፍጥነት መጠን በሚፈለገው ልክ ሊሆን አልቻለም። ስለዚህ በፍጥነት ማሽከርከር ምክንያት የሚደርሰው የትራፊክ አደጋ መንስኤ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ይሄ ነው ብሎ አንድ መንስኤ ብቻ ማስቀመጥ አይቻልም። ከአሽከርካሪዎች ሥነ ልቦና፣ ባሕሪይ ሊሆንም ይችላል።

ጥናቱ ሲካሄድ የቆየው በመንገድ ዳር ምልከታ በመሆኑና በፍጥነት ሲያሽከረክሩ የነበሩ አሽከርካሪዎችን የማያካትት በመሆኑ ጥናቱ ጥልቅ የሆነ ከፍጥነት በላይ የማሽከርከርና አደጋ የማድረስ መንስኤው ምን እንደሆነ አይጠቁምም። በአሽከርካሪዎች ሥነ ባሕሪ ዙሪያም ጥልቅ ቃለ ምልልስ አልተደረገም። በመሆኑም በነዚህ የመንገድ ዳር ምልከታዎች ነው ፍጥነት አሁንም የትራፊክ አደጋ ዋነኛ መንስኤ መሆኑ የተለየው።

በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥርና ሁነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ጌታቸው በበኩላቸው እንደሚገልፁት በአዲስ አበባ ከተማ ለትራፊክ አደጋ ትልቁ መንስኤ ፍጥነት መሆኑ በዳሰሳ ጥናቱ ተመላክቷል። የቀበቶ አጠቃቀምም ከሀምሳ በመቶ በታች ነው። የጭንቅላት መከላከያ ቆብም አጠቃቀም አነስተኛ መሆንም ለአደጋው መበራከት አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል።

ነገር ግን 59 ከመቶ የሚሆኑት የከተማዋ አሽከርካሪዎች ከተቀመጠው የፍጥነት ወሰን ገደብ ላይ የሚያሽከረክሩ ናቸው። ለዚህም የፍጥነት ቁጥጥር ሥርዓቱ ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ የንግድ ተሽከርካሪዎች ገቢያቸውን ለማሳደግ በፍጥነት ማሽከርከር እና አርፍዶ ወጥቶ ቶሎ ለመድረስ በፍጥነት ማሽከርከር እንደ ዋና ዋና መንስኤዎች ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር አደጋውን ለመከላከል በይበልጥ መሥራት ያለበት በዚሁ በፍጥነት ላይ ነው።

በፍጥነት ማሽከርከር ምክንያት የሚከሰተውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በከተማዋ በርካታ ቦታዎች ላይ የፍጥነት ቁጥጥር በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንትና በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ይካሄዳል። ይህንኑ የፍጥነት ቁጥጥር ሥርዓቱን ለማሳደግ ራዳሮች ቋሚ ሆነው የሚሰቀሉበትንና ከዛ መረጃ በመውሰድ ቅጣት የማበጀት ሥርዓት ለመዘርጋት እየተሠራ ይገኛል። በተለይ በአዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ የትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል ከተቋቋመ ወዲህ እነዚህን ችግሮች እየቀነሳቸው መጥቷል።

ከዚህ በኋላም ቁጥጥሩ በካሜራ ስለሚሆን ወደ ዘመናዊነት ለመግባት ኤጀንሲው እየተንደረደረ ነው። በዚሁ መንገድ ችግሩ ይፈታል ብሎ ያስባል። በሌላ በኩል ደግሞ በመንገድ ላይ ያሉ የፍጥነት መቀነሻዎች በኮንክሪት ወይም በአስፓልት የተሠሩ ነበሩ። ይሁንና አሁን ከኮንክሪት ወደ ፕላስቲክ እንዲሸጋገሩ ተደርጓል። ይህም ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ ያስችላል ተብሎ ታምኖበታል።

# ዓለም አቀፍ



## የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች ተኩስ ለማቆም ቢስማሙም የተኩስ ድምጽ እየተሰማ ነው ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሱዳን ተፋላሚዎች ከትናንት በስተያ ጠዋት ጀምሮ ለ72 ሰዓታት የሚቆይ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ቢደርሱም በድጋሚ የተኩስ ድምጽ በመስማት ላይ ነው።

በሱዳን የተቀሰቀሰው ግጭት ሀገሪቱ ወደ ዲሞክራሲያዊ የሲቪል መንግስት ለመሸጋገር የምታደርገውን ጥረት የናደ ነው ተብሏል፡፡

የተመድ መልእክተኛ ተኩስ አቁም በከፊል ተግባራዊ መሆኑን እና ሁሉም አካላት እውነተኛ ንግግር ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት የለም ብለዋል። በሱዳን ጦር እና በጀነራል ሀምዳን ደጋሎ በሚመራው የፈጥኖ ደራሽ ኃይል መካከል የተጀመረው ጦርነት አንድ ሳምንት ያለፈው ሲሆን በተለያዩ ጊዜ የተደረጉ የተኩስ አቁም ስምምነቶች ተግባራዊ አልሆኑም።

የቅርቡ በአሜሪካ እና በሳኡዲ አረቢያ አደራዳሪነት የተደረሰው ተኩስ አቁም ሲጀመር ተግባራዊ የነበረ ቢሆንም፤ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አልሆነም። በድጋሚ የተኩስ ድምጾች እየተሰሙ መሆናቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

የካርቱም እህት ከተማ በሆነችው ኦምዱርማን አመሻሽ ላይ የተኩስ ድምጽ ይሰማ እንደነበር ሮይተርስ በዘገባው ጠቅሷል። የሱዳን ጦርም በሱዳን ሶስተኛ በሆነችው ባህሪ ከተማ ከሚገኘው የነዳጅ ማጣሪያ ታጣቂዎችን ለማባረር ድሮን ሲጠቀም ነበር ተብሏል።

የተመድ የሱዳን ልዩ ተወካይ ፐርተስ ሁለቱም ተፋላሚ ኃይሎች ለእውነተኛ ንግግር ዝግጁ አለመሆናቸውን እና ተኩስ አቁሙም በተወሰነ ቦታ ተግባራዊ መሆኑን ተናግረዋል። ፐርተስ ይህ የተሳሳተ ስሌት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በሱዳን የተቀሰቀሰው ግጭት ሀገሪቱ ወደ ዲሞክራሲያዊ የሲቪል መንግስት ለመሸጋገር የምታደርገውን ጥረት የናደ ነው ተብሏል። ሀገራት በሱዳን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዲፕሎማቶቻቸውን ለማውጣት በጥድፊያ ላይ ናቸው ሲል አል አይን ኒውስ ገልጿል።

## ስዊድን የተኮሰችው ሮኬት በስህተት ጎረቤቷን ኖርዌይን መታ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የስዊድን ስፔስ ኮርፕ(ኤስኤስሲ) ከኢስራንጅ የስፔስ ማዕከል የተኮሰው ሮኬት 15 ኪ.ሜ ኖርዌይ ውስጥ ከተጓዘ በኋላ ተበላሽቶ ተከስክሷል። በጉዳዩ ላይ ከስዊድን ባለስልጣናት በይፋ እንዳልተነገረው የኖሮዌይ ውጭ ሚኒስቴሩ ገልጿል፡፡

በሙከራው ሮኬቱ 250 ኪሎ ሜትር በመጓዝ የመሬት ስበት ዜሮ በሆነበት ርቀት ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ኤስኤስሲ ኃላፊ ፊልፕ ኦህልሰን እንደገለጹት፤ አንድ ሺህ ሜትር ከፍታ ባለው ተራራማ ቦታ አርፏል። ኃላፊው እንዲህ አይነት ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል እና ሁነቱን ለስዊድን እና ለኖርዌይ መንግስት ማሳወቃቸውን ተናግረዋል።


ኤስኤስሲ ሮኬቱ ለምን በተሳሳተ አቅጣጫ እንደሄደ ለማወቅ ምርመራ ተጀምሯል ብሏል። የኖርዌይን ውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ በኖርዌይ ድንበር በኩል የሚደረጉ እውቅና የሌላቸው እንቅስቃሴዎችን በጥብቅ እንደሚከታተሏቸው ገልጸዋል።

በጉዳዩ ላይ ከስዊድን ባለስልጣናት በይፋ እንዳልተነገረው የኖሮዌይ ውጭ ሚኒስቴሩ ገልጿል። የድንበር ጥሰት



ሲያገጥም ኃላፊነት ያለባቸው የኖርዌይ የውጭ ጉዳይን ጨምሮ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ እንዳለባቸው ሮይተርስ ዘግቧል።

# ስፖርት



# አንጋፋው አትሌት የህይወት ታሪኩ ላይ ያተኮረ መጽሐፉን አስመረቀ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚያሳዩት አቋም ሃገርን ከማኩራት አልፎ የሌላውን ዓለም ህዝብም ማስደመሙ ግልጽ ነው።በዚህም ምክንያት በአትሌቶቹ ስም ሃውልት ከማቆምና ስፍራዎችን ከመሰየም ባለፈም በህይወት ታሪካቸው፣ በገድላቸውና የሩጫ ህይወታቸው ላይ ያጠነጠኑ መጽሃፍቶችን ይደርሳሉ፤ ፊልሞችንም ይሰራሉ።በአንጻሩ ይህ ዓይነቱ ልምድ እምብዛም ባልተለመደበት ኢትዮጵያ የጥቂት አትሌቶችን ህይወትና ተሞክሮ የሚዳስሱ መጽሃፍት በሌሎች ጸሃፊዎች ተዘጋጅተዋል።

በዚህም ረገድ ፈር ቀዳጅ ሊባል የሚችልና ለሌሎች አትሌቶችም አርዓያ የሚሆን የአንጋፋው አትሌት የህይወት ታሪክ በመጽሃፍ መልክ ተዘጋጅቶ ለአንባቢያን ቀርቧል።‹‹የተፈተነ ጽናት›› በሚል ርዕስ የታተመውና የ286 ገጽ ብዛት ያለው ይህ መጽሃፍ፤ በተለይ በማራቶን ሩጫ ስኬታማ፣ ለሃገሩም ኩራት መሆን በቻለው አትሌት መቶ አለቃ በላይነህ ዴንሳሞ የተጻፈ ነው።በግራንድ ኃይሌ ሆቴል በነበረው የመጽሃፉ ምረቃ መርሃ ግብር ላይም የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ጨምሮ አትሌቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።




አንጋፋው አትሌት በመላው ዓለም የናኘ ዝናውንና በአትሌቲክስ ስፖርት እጅግ ፈታኝና ከፍተኛ ጽናትን በሚጠይቀው ማራቶን ስኬታማ ለመሆን ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች ጨምሮ ህይወቱ ያለፈባቸውን መንገዶች መጽሃፉ ይተርካል።በዚህም ጀማሪና ወጣት አትሌቶች ልምድ የሚያገኙበትና ብርታትንም ሊሰንቁ የሚችሉበት ይሆናል።መጽሃፉን ያነበቡ የደራሲው አጋሮችና የተለያዩ ባለሙያዎችም ለወጣት አትሌቶች መነሳሳትን የሚፈጥርና ለሃገር የሚከፈልን መስዋዕትነትንም የሚያሳይ ስለመሆኑም ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ኢትዮጵያን ካስጠሩ ጀግና አትሌቶች መካከል ቀዳሚ የሆነው አንጋፋው ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፤ ወደ አትሌቲክስ ስፖርት ከመግባቱ አስቀድሞ እንደ አርዓያ ከሚመለከታቸው አትሌቶች መካከል አንዱ መቶ አለቃ በላይነህ ዴንሳሞ እንደነበር ይገልጻል።ልምምድ በሚያደርግበት ወቅት የሚመለከተው ሲሆን፤ በአንድ ወቅት ከዓለም አቀፍ ውድድር መልስ ይዞለት የመጣው ትጥቅ (የስፖርት ሱሪ እና ጫማ ድጋፍ) ትልቅ መበረታቻ እንደሆነው አስታውሷል።በላይነህ ለሃገሩ ኢትዮጵያ ጽኑ ፍቅር ቢኖረውም በአንዳንድ ሁኔታዎች ለዓመታት ኑሮውን በባህር ማዶ አድርጎ ቆይቷል።ከአሁን በኋላ ግን ባኮራት ሃገሩ መኖር እንደሚገባው በመግለጽም ለዚህ ይረዳ ዘንድ 10 መጽሃፍቶች እያንዳንዳቸውን በ10ሺ. ብር ሂሳብ በአጠቃላይ በ100ሺ. ብር በመግዛት ቀዳሚ ተግባርም አከናውኗል።

ሌላው የቀድሞ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን አባልና በማራቶን ሃገሩን ከረጅም ዓመታት በኋላ በኦሊምፒክና ዓለም ቻምፒዮና መድረክ ውጤታማ ያደረጋት አንጋፋ አትሌት ገዛኸኝ አበራም ከበላይነህ ባገኘው ስልጠና፣ ልምድና ምክር ታግዞ ውጤታማ እንደሆነ ገልጿል።የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት የሆነው ገዛኸኝ በግሉ የ50ሺ. ብር መጽሃፍ ገዝቷል።ስራ አስፈጻሚውም ተወያይቶ አትሌቱን ለማበረታታት እንዲሁም በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ተቋማት ታዳጊዎች መማሪያ እንዲሆናቸው የ200ሺ. ብር ግዢ እንደሚፈጽምም ጠቁሟል።

የበላይነህ የቀድሞ ክለብ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን (ኮሜድላን) በመወከል የተገኙት ነብዩ ኢሳያስ፤ አትሌቱ ለአባላቱ አርዓያ እና በስነምግባር የታነጸ አመራር እንደነበረም አስታውሰዋል።የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፤ መጽሃፉ ሌሎች አትሌቶችም አርዓያነቱን እንዲከተሉ እንደሚያነሳሳ ጠቁመዋል።አትሌቱ በርካታ ስራ ማከናወን የሚችል በመሆኑም ቀጣይ ህይወቱን በሃገሩ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል።

በምረቃ ስነስርዓቱ ላይ የተገኙት የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ፤ አትሌቱ ወደ ክልሉ ተመልሶ ወጣት አትሌቶችን የሚያበቃበትን መንገድ እንዲያመቻች ጠይቀዋል።ለዚህም ይረዳው ዘንድ በሀዋሳ ከተማ ዓይን ቦታ ላይ 1ሺ. ካሬ ሜትር ቦታ የክልሉ መንግስት እንዳበረከተለት ገልጸዋል፡፡

ከመጽሃፉ ሽያጭ 20 ከመቶ የሚሆነው ለመቄዶንያ እርዳታ ድርጅት የሚውል ሲሆን፤ ሌሎች የአትሌቱ ወዳጆችና አድናቂዎችም መጽሃፉን በከፍተኛ ዋጋ ገዝተዋል።

ከምርጥ የማራቶን አትሌቶች መካከል አንዱ የሆነው መቶ አለቃ በላይነህ ዴንሳሞ በተለይ በሮተርዳም ማራቶን ባስመዘገበው የዓለም ክብረወሰን ይታወቃል።በፖርቹጋላዊው አትሌት ለሶስት ዓመት ተይዞ የቆየውን ክብረወሰን 2:06:50 በመሮጥ ያሻሻለ ሲሆን፤ ለ10 ዓመታት ያህል ሳይደፈር መቆየቱም አስደናቂ አድርጎታል።


## የጨረታ መዝጊያ እና መክፈቻ ቀን ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር DCE/SF/42/2023

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለጃንሜዳ ስታፍ ኮሌጅ ግንባታ ፕሮጀክት አገልግሎት የሚውሉ “Supply and Fix Epoxy Floor Finish” ግዥ ለመፈጸም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ መጋቢት 17/2015 ዓ.ም ማውጣቱ የሚታወስ ሲሆን በማስታወቂያው መሰረት ጨረታው ሚያዝያ 12/2015 ዓ.ም እንደሚከፈት ተገልፆ ነበር።

ይሁን እንጂ ጨረታውን ማራዘም በማስፈለጉ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን እንደሚከተለው የተራዘመ መሆኑን እንገልፃለን።

**ጨረታው :- ሚያዝያ 25/2015 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ይዘጋል።**

**ሚያዝያ 25/2015 ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት ይከፈታል።**

**ማሳሰቢያ፡-** ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ከጨረታው መዝጊያ ቀንና ስዓት በፊት ወይም በዕለቱ እና በሰዓቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

**አድራሻ፡- የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**

**የቀጥታ ስልክ ቁጥር 0114-40-34-/34**

**ማዞሪያ 0114-42-22-70/71/72**

**ፖ.ሳ.ቁ 3414**

**ፋክስ ቁ. 0114-40-04-71/0114-42-07-46**

**ኢትዮ ቻይና ወዳጅነት ጐዳና**

**ድረ ገፅ ፡-WWW.dce.gov.com/www.dce.et.com**

**ኢሜል፡-INFO @dce-et.com**

## የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ

## ድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የጋም/ሕ/ብ/ክ/መንግሥት ትም/ቢሮ በSDG (በዘላቂ ልማት ግብ) በጀት ድጋፍ በ2015 ዓ.ም በጀት ዘመን ጎግ ወረዳ፣ ታታ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት፡- አኮቦ ወረዳ ካንካን 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት፡- ጋምቤላ ወረዳ ሲሪ ማጀንግር፣ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት መንገሺ ወረዳ ዲፓ 2ኛ ትም/ቤት፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ ዋንኬ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ሶላር ግዥና ተከላ (SUPPLY AND INSTALLATION) በግልፅ ጨረታ ተጫራቾችን አወዳድሮ ለመግዛትና ለመትከል ይፈልጋል።

**በዚሁ መሠረት፡-**

1. የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው።
2. የምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ የሚችል።
3. የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል።
4. ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
5. 2015 ዓ.ም ከውዝፍ ግብር ነፃ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
6. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 (አስራ አምስት) ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ዘወትር በስራ ሰዓት ቢሮ ቁጥር 20 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ::
7. ተጫራቾች የጨረታውን ዋስትና ማስረከቢያ 1% ሲፒኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ብቻ ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
8. ተጫራቾች ጨረታውን ዶክመንት ዋጋ ዋናውንና ኮፒ ሁለት (2)ኮፒዎችን ለየብቻ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ምዝገባ በ16ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ አስገብተው ጨረታው በዚሁ ዕለት በ4፡00 ሰዓት ላይ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቦታ ይከፈታል፡፡

ቢሮው የተሻለ አጫራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር፡ 0475510136**

## የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ